# ምዕራፍ አምስት

ገብረብሩክ ወደላይ ወደታች ወደ ግራ ወደ ቀኝ ብሎ ወ/ሮ አረጋሽን አሳምኖ ቤታቸውን መሸጥ ፈጽሞ አልቻለም:: ወደ ሚቀጥለው ፕላኖቹ ለማስኬድ የሚያስችሉትን ቅድመ ዝግጅቶች ግን አጠናቋል:: ከተሳካለት ምግቧን መመረዝ፣ ወይም እተኛችበት አፍኖ በመግደል አጠገቧ ሴቶች ጽንስ ለማበላሸት የሚውጡትን ኪኒን ከመኝታዋ አጠገብ ማስቀመጥ፣ አለበለዚያ ከቀጭ በሉዎች ጓደኞቹ ጋር በመመካከር መኪና ተከራይተው ተከታትለው አመች ቦታ ላይ መግጨት፣ ካልሆነ ካልሆነ ደግሞ ከነመረቁ ጭንቅላቷን መፈርከስ ነው" ብሏል::

ነቢዩ ትርሲትን ባልቻ ሆስፒታል ካስገባ በሁዋላ፣ ብዙም ሳይቆይ ወ/ሮ አረጋሽ ጋ በመደወል የጥቁር አንበሳ ጉዞዋን ሁኔታ ጠየቃት:: "ሰማይ ዝቅ ምድር ከፍ ብትል ቤቴን ጥዬ የትም አልሄድም" ስትል ፍርጥም ብላ በመወሰኗ ልዩ ጥንቃቄ እንድታደርግ እየመከራት ሌላ መስመር ስለመጣበት የሷን መስመር ዘጋው::

ወ/ሮ አረጋሽም የገብረብሩክ መቁነጥነጥ ስላላማራት ገብረብሩክ የማያውቀው የዛሬ 30 ዓመት ወደ ውጪ ተልከው



ከነበሩት ህጻናት አንዱ የሆነው የአጎቷ ልጅ ደረጀ ከውጪ ከመጣ ጀምሮ ሥራም ስለሌለው በቤቷ ውስጥ ስለተፈጠረው ሁኔታ በደምብ አስረድታው ዘመዴ ብላ ሳይሆን ቤት የሚጠርግ፣ መኪና የሚያጥብና የመሳሰሉትን የሚያግዝ በማለት እቤቷ አምጥታው በተለይ ገብረብሩክን ሲያይ "ምን ልሁንልህ" እያለ ለማስደሰት ደፋ ቀና ስማለት ተዘጋጅቷል:: ደረጀ እውጪ በቆየባቸው ዓመታት ሚሊቴሪ ሳይንስ ሲያጠና በጎን በኩል ማርሻል አርት ተምሮ ብላክ ቤልቱን በከፍተኛ ማዕረግ አግኝቷል:: ልብ ብሎ ላስተዋለው የቅጥነቱ፣ የቁመቱ አጠር ማለት እንኳንስ ሁለትና ሦስት ሰዎችን የሚያጋድም ደህና ትንፋሽ የሚያወጣ፣ ሰው እፍ ቢለው የሚወድቅ ነው የሚመስለው:: ፈገግታውና ትህትናው ግን እንኳንስ የሰው ፍጥረት የውሾችን ጭራም ያስቆላል::

ገና ሰላምታ እንኳን ሳይሰጣት ገብረብሩክ ከውጭ እንደገባ "ምንድን ነው ይኸ ደግሞ ጥውልግልግ ያለ አሳዛኝ ነገር፣ ከየት አመጣሽው ልጄ? " ሲላት ብልጭ አለባትና "የጋጣሚ ነገር ሆነና አንዱ ከፍ ሌላው ዝቅ ያለ ኖሮ ስለኖረ እንጂንተ አይነቱ ቀፎ ክብሩን የሰው ፍጥረት እንዲህ ሲስዘልፈው ይታያል፣ ይሁን አላማ ማወቅህ ነው፣ ለመሆኑ ያንተን ሴሰኝነት የረከሰ ስሜትህን የምትወጣበት ሌላ አደራ የሚስጥህ ስላጣህ እኔ አፈላልጌ እንዳመጣልህ ትጠብቅ ኖሯል? እስቲ እንግዲህ ወንዱን አንቀህ ስሜትህን ትወጣበት እንደሆነ ስማየት ያብቃን በዓለም ላይ እየበዙ የመጡት ወንድ ከወንድ ጋር የሚጋቡት አይነት እኔ በሌለሁበት እዚህ ልጅ ጋር ትንንቅ ብትጀምር እሱም አንደ ትርሲት የዋህ እንዳይመስልህ::

የአንተን አይነት አራት ወይም አምስት የሚሰባብር ነው:: ተሳክቶልህ ብትደፍረው መንግሥትም የገባህበት ገብቶ አንገትህን ሕዝብ ፊት ነው የሚቆርጠው::

ምናልባት ርኩሱ መንፈስህ አስቦት ከሆነ በዚች በተቀደሰች ምድር በኢትዮጵያችን ውስጥ ወንድ ከሴት ጋር መጋባት እንጅ ወንድ ከወንድ፣ ሴት ከሴት ጋር አይታሰብም፣ አይሞከርም በልና ንገረው ርኩሱን መንፈስህን" ልትለው ስታወጣና ስታወርድ ነበር "አንችን አኮ ነው የማነጋግረው" ብሎ ሲጮህባት ከሃሳቧ የባነነችው፤ አስተያየቷና አቋቋሟ ስላላማረው ሌላ ቃል ሳይተነፍስ ከአጠገቧ ተስፈነጠረ::

ሰሞኑን ተፈሪን ፈልጎት በማጣቱ ገብረብሩክ ተሰፋ ቆርጦ በራሱ ብቻ ስለሚያደርገው እያወጣና እያወረደ ሳለ ሌላው ጓደኛው ደውሎ "ስማ ገብረብሩክ ሰሞኑን ተፈሪ ከማን ጋር እንደታየ ብነግርህ እኔን ወረኛ ከማለት በስተቀር ፈጽሞ ልታምነኝ አትችልም::" ሳይጨርሰው "ለመሆኑ ከማን ጋር ታይቶ ነው እንዲህ የምታጋንነው?

"አይ! አይ! ይቅርብህ" ሲለው ገብረብሩክ ከው ብሎ "አንተ ትሰማለህ፤ እኔ ነኝ መናደዴንም መደሰቴንም የምወስነው፤ ከነገርከኝ ንገረኝ፣ ካልነገርከኝም ደህና ሁን" ብሎ ስልኩን ሊዘጋው ሲል "ቆይ ቆይ እኔው ላንተ አስቤ ነውኮ፣ ከማን ጋር መስለህ እየታየ ያለው፣ 'ከኮብራ' ጋር እኮ ነው"::

ቀጭ በሉዎች ሙሰናዎች፣ በአጠቃላይ ህግ ጣሽዎች ገብራይን 'ኮብራ' ብለው ነው የሚጠሩት:: "እንኳን ነገርከኝ" ብሎ ስልኩን ዘጋው:: ብዙም ሳይቆይ ተፈሪን ደጋግሞ ደወለለት:: መልስ ግን የለም:: ይህችስ ሁኔታ ማደር መዋል



የለባትም በማለት ተፈሪን ለማግኘት ነጋ ጠባ ደፋጣ ማካሄድ ሆነ:: ገና ከእንቅልፉ ሲነቃ ያንቃጨለው ስልክ የተፈሪ ነበር:: በጣም እንደናፈቀው ዘመድ ሞቶበት በድንገት ገጠር ሂጆ ስለነበረ ነው የጠፋሁብህ አለው:: "አይ ምንም አይደል መች እንገናኝ አባክህን?

"በፈለከው ሰዓት"

"የት?"

" እዚያው እተለመደው ቦታ" ልክ በተባባሉበት ቦታና በሰዓቷ እንደተገናኙ ገብረብሩክ በተፈሪ ላይ ያለውን ጥላቻና ብሶቱት ፍጽሞ ሊደብቀው ባለመቻሉ ትንንሽ ህይኖቹ ወዲይ ወዲህ ሲንከባለሉ ተፈሪን "ንቅቸብሃለሁ አንተ ከሃዲ" የሚሉት ይመስላሉ::

እነ ገብራይ ከተፈሪ ጋር በተቀጣጠሩበት ተመሳሳይ ቦታ እኩል አልደረሱም:: የግብረብሩክ ሁኔታ ስላላማረው ኧረ ድረሱልኝ ብሎ ሊጠራ ትንሽ ነው የቀረው::

"ለመሆኑ" አለው ገብረብሩክ በድንገት "እውነት ዘመድ ሞቶብህ ነው የጠፋኸው? ኮብራንስ አግኝተኸው ታውቃለህ? ሞኝህን ፈልግ፣ ለካስ ልቤን ሁለመናዬ ወዳጄ ብዬ አምኘ ስጥቼህ አንተ ኖረሃል ሥራዬንም እንጻጣ ያደረከኝ፣ እነ ስላለንም ከሥራ ያስባረርካቸው፣ ኧረ ስንቱን ላውራው፣ የእኔን ህይወት አበላሽተህ፣ አንተ ተሹመህ ተሽልመህ ለመኖር ታስቦ ይሆናል:: ይህች ቦታ ስንት ነገር ሠርተንባታል:: ፀጥታዋ ደስ ትላለች:: አይደለም? እኔን ብቻ ሳይሆን ቦታዋንም ስለካድካት ፈርዳብሃለች ላንተ ሲያንስህ ነው" ብሎ በግንባሩ ላይ ተኮሰበት በረረ::

እነ ገብረ-ይ ከተቀጣጠሩበት ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች አረፋፍደው በቀጠሯቸው ቦታ ሲደርሱ ተፈሪ የወደቀበት አካባቢ በደም ተለውሶ እስከ ዘላለም አሸልቧል:: ብዙም ጊዜ ሳያጠፉ ሊላም ሃይል ጨምረው ወደ ባልቻ ሆስፒታል ወደ መኖሪያ ቤቱ ወደ ነቢዩ ቢሮ ባጠቃላይ ገብረብሩክ ጥቃት ሲያደርስባቸው ይችላል ብለው ወደሚፈሯቸው ቦታዎች ሁሉ ሃይል አስማሩ:: ገብረብሩክ በቀጥታ ያመራው ወደ ነቢዩ ቢሮ ነበር:: እቢሮው እንደደረሰ ጸሃፊው ስብሰባ ላይ መሆኑን ስለነገረችውና ግራና ቀኝ ያለው ግርግር ስላላመቻቸው ሌላ ጊዜ እመጣለሁ ብሎ ሌላ ስም ነግሯት ተፈትልኮ ወጣ::

መክብብ በተለይ ብቻውን ሲሄድ ቢያገኘው እራት እይን እንዳለው ነው የሚሆነው:: ገብረብሩክ ወይም ቁጭ በሉዎች ባገኙት ቦታ እንደሚተናኮሉት ምንም ጥርጣሬ የለውም:: "ቁም እንዳትበላሽ" ብሎ ፊቱን ጥቁር የኔ ቢጤ ከረጢት የሚመስል ነገር ጭንቅላቱ ውስጥ አጥልቀው፤ ገመድ እንገቱ ውስጥ አስገብተው መኪናቸው ውስጥ ገፋፍተው ጨምረው ወደ አንዳቸው መኖሪያ ቤት ውስጥ በመውሰድ አስቃይተው የሚገድሉት እየመሰለው ሁሉም በየሄደበት ዙሪያውን ይቃኛል::

የትርሲትን ሁኔታ በባልቻ ሆስፒታል መልክ መልክ ካስያዙ በሁዋላ ትርሲት ለእህቷ ለመላክ ለመክብብ የሰጠችውን ደብዳቤ " ከመላክህ በፊት አንብብና የረሳሁት ነገር ካለ ጨምርበት" ብላው ስለነበር በገጹ መጨረሻ ላይ የሚጨምረውን ከመጨማመሩ በፊት ዋናው ፖሲታ ቤት



እንደደረሰ የሚወዱትን ሰው መሞት፤ በደብዳቤ እንደማርዳት አይነት ወይም ስለሚያሳዝን ታሪክ የተጻፈን እንደሚያነብ አይነት ተራኪ ድምጹን ከፍና ዝቅ እያደረገ

"**እጅግ በጣም የምወድሽ** የምትናፍቂኝ ውድ እህቴም ጓደኛም ሁሉንም የሆንሽው ፍርዬ እንደምን አለሽልኝ? ጊዜሽን የኔንም ያንቺንም ለመቆጠብ አንቺም መስማት እኔም መናገር ወደምፈልገው ነጥብ በቀጥታ ላስገባሽ::

ከሁሉም በፊት ግን ማለት የምፈልገው ህይወቴ እስከዛሬ ሊቆይ የቻለው ያንቺ በህይወት መኖር ነው:: የነፍሴ የህይወቴ እመቤት ነሽ:: ግልጽ ላድርግልሽ፤ በእርግጥ ስናድግም ቶሎ ተሰፋ ቆራጭ እንዳንሆን እየተመከርን ነው ያደግነው:: እስከ ህልፈተ ህይወታችን እንደተፋጨረጨርን ነው ህይወታችን የምታልፈ::ተስፋ ቆርጦ መሞት ያው እንደሚባለው ሌላ ተጨማሪ ሞት ነው፡ ይባል የል፡ እናም አንቺ ባትኖሪ ኖር እኔም ገና ድሮ ራሴን ለማጥፋት ወስኘ ነበር:: ገመድ ማማረጡ፤ በረኪና ጠንካራውን ከስሰላሳው መስየቱ፤ ኪኒን ከመጠን በላይ ስለመውሰዱ፤ ከፎቅ ላይ ስለመከስከሱ፡ ...ምን ያላሰብኩት ራሴን የማጥፊያ መንገድ አለ ብለሽ? ይህን ሁሉ አወጣ እወርድና ውይ በስመ እብ፤ እኔን ብቻ ሳይሆን እህቴንም እኮ ነው የምገድለው እላለሁ::

እኔ አንድ ነገር ብሆን ሀዘኑ እንድ ሳይሆን ለቁጥር የማይመች የከበደ፤ ያውም በጀርመን አገር ከሃዘን ሁሉ የከፋ ሃዘን እንደሚሆንብሽ በመገንዘብ ህይወቴን ለኔ ብዬ ሳይሆን ላንቺ ብዬ ይኸው ይህቺን ደብዳቤ ሁሉ ለመጻፍ በቃሁ:: የሚገርምሽ በህይወት ለመቆየቴ የመክብብም እስተዋጽኦ

አለበት። አንድ ቀን ባይገርምሽ ያ ጭራቅ የደፈረኝ ሰሞን ገና ማርገዜን እንዳወኩት ከመክብብ ጋር ቀጭ ብለን ስንጨዋወት ሁለታችንም እንባችንን እያፈሰስን እኔ በድንገት 'ስማ መክብብ አሁን በእኔና በህይወት በሌለ ሰው መካከል ምን ልዩነት አለ? እኔ እኮ ዝም ብዬ ነው ቦታ የማጣብበው" ስለው እንዴት እንደደነገጠ፣ እንዴት እንደለመነኝ 'ምነው ትርሲትዬ እኔ እኮ እህት የለኝም፣ ማን ጓደኛ ሊሆነኝ? አምላካችን እሱ እንደፈጠረን እሱ የሚያደርገውን ያድርግ እንጅ በፈጣሪ ሥራ መግባትማ ትልቅ ስህተት ነው፣ በይ 'የሠይጣን ጆሮ ይደፈን' ያለኝን እያስታወስኩ ለንት ጊዜ እራሴን ከመጉዳት ታቅቢያለሁ መሰለሽ።

በነገራችን ላይ መክብብ እንደሰው ሳይመቸው በራበው ሰዓት ምግብ ሳያገኝ መተኛት፣ ባሰኘው ሰዓት ሳይተኛ ለማንበብ የፈለገውን መጽሃፍ ፈልጎ እያጣ ተሰፋ ባለመቁረጥ ትምህርቱን ገፍቶ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርቱን በከፍተኛ ውጤት አልፎ ወደ ዩኒቨርሲቲ ከመግባቱ በፊት ወደ ሽንኩሬ አያቶቹን ሲያስተዋውቀኝና አገር እስጎብኝቶ የዮሐንስንም ጠብል ሊያስጠምቀኝ ለመሄድ እየተዘጋጀን ነው። ገንዘብ በ[illegible] ነው እንዳታስቢ! ለመክብብም የደስ ደስ እያሉ በተለይ ቀደም ብለው የተማሩት ደህና ደህና ደሞዝ ያላቸውና ነጋዴዎች ሽንኩሬዎች አሁን አሁን ጎበዝ ተማሪ እያፈላለጉ መክብብም የዚሁ እጣ ደርሶት ገንዘብ እንደልባችን ነው።

ጽንሱን በተመለከተ የሚሰማኝን ስሜት ለወላጆች ሳማክር 'እኔ እንደዚህ አድርጎኝ አያውቅም' ነው የሚሉኝ፣ ሃኪም ጋ ስሄድ 'ወድቀሽ ነበር..ምናምን ግጭቶሽ ነበር፣ ትንሽ



ጊዜ አይተነው ወደ ስፔሻሊስት ጋ እንልክሻለን..ምንትሴ' ከማለት በስተቀር ሌላ የረዱኝ ነገር የለም። በተለይ ወድቀሽ ነበር ምናምን ገጭቶሽ ነበር ሲሉኝ ሁለመናዬ ቅጥል ብሎ ጽንሱም እንደተበሳጨ ሰው ሲገላበጥ ይሰማኛል። ያኔ በሃይል ነው የሚወጋኝ። ያው እንግዲህ መክብብ እንዳለው በእግዜር ሥራ አንግባ ነው። የሚሆነውን እብረን እናያለን።

ፍርዬ፣ እናታችን ምንኛ ጻድቃን ሰው ነች። ይህን ሁሉ ጉድ ሳታይ ህይወቷ ማለፉ፣ አሁንስ ቀናሁባት። ይህንንም ስልሽ ተስፋ የቆረጥኩ እንዳይመስልሽ፣ አይዞሽ ወኔው እንዳለ ነው። ማለት ስላለብኝ ነው ያልኩት።

እናማ ይኸውልሽ ከምኖርበት ቤት አደራ በሊታው ገብረብሩክ የአባታችንን ንብረት ስመብላት ለመዝረፍ ሲል የተጠቀመው ዘዴው ሁሉ ደግመው ሲናገሩት የባሰ የንዴት ሰዓትን መጨመር ነው፣ ብተወው ይሻላል። መክብብ በሚጠራቸው እኔም ልጥራቸው፣ 'ቀጭ በሉ' የጭራቁ ጓደኞች ነጭ ለባሽ የፖሊስ ባልደረቦች መስለው እቤት መጡ። መክብብን ራሱን እስከሚስት ደብድበው ጣሉት። እኔንም ያው ከምኖርበት ከኢምፔሪያል ሆቴል ጀርባ እስከ ፈረንሳይ ኤምባሲ አካባቢ ወስደው ጸጥ ረጭ ያለ ቦታ ሲያገኙ የቻሉትን ያክል ከቀጠቀጡኝ በሁዋላ ጥለውኝ ሄዱ። የእግዚአብሄር ፈቃድ ሆኖ ቀይቼ ነቃሁ። የሚገርምሽ ያኑ እስት ወይም በማግስቱ ልንቃ እስካሁን ለይቼ አላውቅም። ፈረንሳይ ለጋሲዮንንን አካባቢ ያሉ ወጣቶች ማታ ከት/ቤት ሲመለሱ ማቃስቴን ሰምተው ተረባርበው እዚያው አካባቢ ያለ የግል ጤና ጣቢያ ወስደው ካስተኙኝ በሁዋላ የእማዬ የክርስትና ልጅ ጋ ስልክ

አለበት፡፡ አንድ ቀን ባይገርምሽ ያ ጭራቅ የደፈረኝ ሰሞን ገና ማርገዜን እንዳወኩት ከመክብብ ጋር ቁጭ ብለን ስንጨዋወት ሁሰታችንም እንባችንን እያፈሰስን እኔ በድንገት 'ሰማ መክብብ አሁን በእኔና በህይወት በሌለ ሰው መካከል ምን ልዩነት አለ? እኔ እኮ ዝም ብዬ ነው ቦታ የማጣብበው" ስለው እንዴት እንደደነገጠ፣ እንዴት እንደለመነኝ 'ምነው ትርሲትዬ እኔ እኮ እህት የለኝም፣ ማን ጓደኛ ሊሆነኝ? እምላካችን እሱ እንደፈጠረን እሱ የሚያደርገውን ያድርግ እንጅ በፈጣሪ ሥራ መግባትማ ትልቅ ስህተት ነው፣ በይ 'የሠይጣን ጆሮ ይደፈን' ያለኝን እያስታወስኩ ስንት ጊዜ እራሴን ከመጉዳት ታቅቢያለሁ መሰለሽ፡፡

በነገራችን ላይ መክብብ እንደሰው ሳይመቸው በራበው ሰዓት ምግብ ሳያገኝ መተኛት፣ ባሰኘው ሰዓት ሳይተኛ ለማንበብ የፈለገውን መጽሃፍ ፈልጎ እያጣ ተስፋ ባስመቁረጥ ትምህርቱን ገፋቶ የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርቱን በከፍተኛ ውጤት አልፎ ወደ ዩኒቨርሲቲ ከመግባቱ በፊት ወደ ሸንኮራ እያቶቹን ሊያስተዋውቀኝና እገር አስጎብኝቶ የዮሐንስንም ጠብል ሊያስጠምቀኝ ለመሄድ እየተዘጋጀን ነው፡፡ ገንዘብ በሽ ነው እንዳታስቢ! ለመክብብም የደስ ደስ እያሉ በተለይ ቀደም ብለው የተማሩት ደህና ደህና ደሞዝ ያላቸውና ነጋዴዎቹ ሸንኮሬዎች እሁን እሁን ጎበዝ ተማሪ እያፈላለጉ መክብብም የዚሁ እጣ ደርሶት ገንዘብ እንደልባችን ነው፡፡

ጽንሱን በተመለከተ የሚሰማኝን ስሜት ስወላጆች ሳማክር 'እኔ እንደዚህ አድርጎኝ አያውቅም' ነው የሚሉኝ፡፡ ሃኪም ጋ ስሄድ 'ወድቀሽ ነበር...ምናምን ግጭቶሽ ነበር፣ ትንሽ



ጊዜ እይተነው ወደ ስፔሻሊስት ጋ እንልክሻለን..ምንትሴ' ከማለት በስተቀር ሌላ የረዱኝ ነገር የለም፡፡ በተለይ ወድቀሽ ነበር ምናምን ገጭቶሽ ነበር ሲሉኝ ሁለመናዬ ቅጥል ብሎ ጽንሱም እንደተበሳጨ ሰው ሲገላበጥ ይሰማኛል፡፡ ያኔ በሃይል ነው የሚወጋኝ፡፡ ያው እንግዲህ መክብብ እንዳለው በእግዜር ሥራ እንግባ ነው፡፡ የሚሆነውን እብረን እናያለን፡፡

ፍርዬ፡ እናታችን ምንኛ ጻድቃን ሰው ነች፡፡ ይህን ሁሉ ጉድ ሳታይ ህይወቷ ማለፉ፡፡ እሁንስ ቀናሁባት፡፡ ይህንንም ስልሽ ተስፋ የቆረጥኩ እንዳይመስልሽ፣ አይዞሽ ወኔው እንዳለ ነው፡፡ ማስት ስላስብኝ ነው ያልኩት፡፡

እናማ ይኸውልሽ ከምኖርበት ቤት አደራ በሊታው ገብረብሩክ የእባታችንን ንብረት ለመብላት ለመዝረፍ ሲል የተጠቀመው ዘዴው ሁሉ ደግመው ሲናገሩት የባሰ የንዴት ሰዓትን መጨመር ነው፣ ብተወው ይሻላል፡፡ መክብብ በሚጠራቸው እኔም ልጥራቸው፣ 'ቁጭ በሉ' የጭራቁ ጓደኞች ነጭ ለባሽ የፖሊስ ባልደረቦች መስለው እቤት መጡ፡፡ መክብብን ራሱን እስከሚስት ደብድበው ጣሉት፡፡ እኔንም ያው ከምኖርበት ከኢምፔሪል ሆቴል ጀርባ እስከ ፈረንሳይ ኤምባሲ አካባቢ ወስደው ጸጥ ረጭ ያለ ቦታ ሲያገኙ የቻሉትን ያክል ከቀጠቀጡኝ በሁዋላ ጥለውኝ ሄዱ፡፡ የእግዚአብሄር ፈቃድ ሆኖ ቆይቼ ነቃሁ፡፡ የሚገርምሽ ያኑ እለት ወይም በማግስቱ ልንቃ እስካሁን ለይቼ አላውቅም፡፡ ፈረንሳይ ለጋሲዮንንን አካባቢ ያሉ ወጣቶች ማታ ከት/ቤት ሲመለሱ ማቃስቴን ሰምተው ተረባርበው እዚያው እካባቢ ያለ የግል ጤና ጣቢያ ወስደው ካስተኙኝ በሁዋላ የእማዬ የክርስትና ልጅ ጋ ስልክ

ደውዬላቸው መጥተው ወስዱኝ። እነሱ ጋ ተደብቄ ከረምኩ። አሁን ደግሞ ይኸው እድሜ ላንቺ አቶ ነቢዩን የመሰለ የሚያኮር ሰው አስተዋውቀሽን ገብረብሩክ በለስ ቀንቶት በውሸት እቀነባብሮ በተረሳና በተደመደመ የኤርትራ ክ/ሀገር ሰበብ ወይም ከተመቸውም እናታችንም የሀረር ሰው ስለሆነች ከሱማሌ ጋር አገናኝቶ ወደ ሱማሌ ትላክ ብሎ ቢያሳስረኝ ጉዳዩ እስከሚመረመር ዋስ ሆኖ የሚያስወጣኝ አለኝ እያልኩ እንዴት በድፍረትና በነጻነት እየኖርኩ መሰለሽ።

ባጭሩ ወ/ሮ አረጋሽ ስለ ጭራቁ ሰምታ፥ ድርጊቱንም አረጋግጣ እየደገሰችለት ነው። እኔንም ካንቺ ባልተናነሰ እየተንከባከበችኝ ነው።

አቶ ነቢዩ ስለገብረብሩክ በሚያስገርም ሁኔታ እኛ ከምናውቀው የበለጠ ብዙ ነገር በመረጃ የተደገፈ፥ ባይገርምሽ የሹራብ ቤታችንን ወደ ራሱ ለማዛወር የሄደበትን አካሄዱ ሳይቀር ሁሉ እጣርቶ ከሚመለከተው ክፍል ጋር ሲነጋገር ከርሞ እኔና መክብብ ለሞኑን ለፖሊስ ቃላችንን እንድንሰጥ ይዞን ሂዷል"፤ ብሎ እንብቦ እንደጨረሰ "ኧ.. ኧ ቆይ፥ ትርሲት ይህን ካለችኝ እይቀር ልጨምርበት" እለና "ታዲያስ ፍርዬ፥ ይኸኛው የእጅ ጽሁፍ ደግሞ የመክብብ ታምራት ነው አለና።

እንደምታስታውሽኝ ተለፋ አደርጋለሁ። ትርሲትዬ ይህን ደብዳቤ ከጻፈችልሽ በሁዋላ እንብበውና የረሳሁት ካለ ጨምርበታን ሳክላት ነበር ያለችኝ። በእርግጥ የረሳችው ምንም ነገር የለም። ደብዳቤውን ከሰጠችን በሁዋላ ግን ፖሊስ ጣቢያ ሂደን ነበር። እናም ዘውትር እንደምትለኝ ለበሳጭና ለደነግጥ ሆዴን በጣም ይቆርጠኛል። እነዚያ እረመኔዎች ያስቃዩኝም



እስካሁን ስሜት አለኝ ትለኝ ነበር። እናም ፖሊስ ጣቢያ ቃሏን እየሰጠች እያለች በጣም ታማብን በእስቸኳይ ሆስፒታል ወስደናት ሆስፒታል እንደደርስንም አቶ ነቢዩ ሳላጋንን ከሉት ሠራተኞች ከግማሽ በላይ ያውቃቸዋልና እስፈላጊው እንክብካቤና ህክምና ተደርጎላት ጽንሱ ተበላሽቶ እሷ ግን ተርፋለች።

ምን ይደረግ እንግዲህ በእግዜር ሥራ ውስጥ መግባት አያስፈልግም። ለማንኛውም ሰሞኑ ሰለምትወጣ አቶ ነቢዩጋ ደውይ ወይም እኛ እንደውላለን።

በተረፈ ስለደህንነታችን ምንም አታስቢ። ባይገርምሽ ገብረብሩክና አጫፋሪዎቹ በቁጥጥር ሥር እስከሚውሉ ጉዳት ሊያደርሱብን ይችላሉ ብሎ ፖሊስ በመጠርጠሩ በህይን ቁራ እየጠበቁን ነው። እኛም የተቻለንን ያህል በግላችን እየተጠነቀቅን ነው። ሽንኩራ ውስጥ ያሉ ታቦቶች እን ለሚያዎች መስሉሽ! ለአቡየ፥ ለመርቆሪዎስ፥ ለጊዮርጊስ፥ ለአማኑኤል፥ ለሚካኤል፥ ለመጥምቁ ዮሐንስ፥ ለክርስቶስ ሰምራ፥ ለተክልዬ፥ ለዶፋው ሚካኤል..ምን ብዬ ልንገርሽ ያልተሳልኩላቸሁ ታቦት የለም። እይን ለአይን ቤተሰባችሁ ሁሉ እንዲተያይ ብዬ፤ ‹‹ ከቶ ለነሱ ምን ይሳናቸዋል››

ምን ጊዜም ያንቺው ወንድማችሁ መክብብ ታምራት ነኝ" ብሎ አሻሽጎ ላከና አካባቢውን እየቃኘ ጉዞውን ቀጠለ።

" የወንደላጤ ነገር፥ ባገኙበት መብላት ባገኙበት ማደር፥ ያዩትን ማሽኮርመም፥ እነእያ እንደልቡ ምን የሚይባሉት አለ››? ይህ አይነቱ የወንደላጤ ባህርይ ገብራይን ሲያልፍም

ደውዬላቸው መጥተው ወስዱኝ:: እነሱ ጋ ተደብቄ ከረምኩ:: አሁን ደግሞ ይኸው እድሜ ላንቺ አቶ ነቢዩን የመሰለ የሚያከር ሰው አስተዋውቀሽን ገብረብሩክ በለስ ቀንቶት በውሸት አቀነባብሮ በተረሳና በተደመደመ የኤርትራ ክ/ሀገር ስበብ ወይም ከተመቸውም እናታችንም የሀረር ሰው ስለሆነች ከሱማሌ ጋር አገናኝቶ ወደ ሱማሌ ትላክ ብሎ ቢያሳስረኝ ጉዳዩ እስከሚመረመር ዋስ ሆኖ የሚያስወጣኝ አለኝ እያልኩ እንዴት በድፍረትና በነጻነት እየኖርኩ መሰለሽ::

ባጭሩ ወ/ሮ እረጋሽ ስለ ጭራቁ ስምታ፣ ድርጊቱንም አረጋግጣ እየደገሰችለት ነው:: እኔንም ካንች ባልተናነሰ እየተንከባከበችኝ ነው::

እቶ ነቢዩ ስለገብረብሩክ በሚያስገርም ሁኔታ እኛ ከምናውቀው የበለጠ ብዙ ነገር በመረጃ የተደገፈ፣ ባይገርምሽ የሹራብ ቤታችንን ወደ ራሱ ለማዛወር የሄደበትን አካሄዳ ሳይቀር ሁሉ አጣርቶ ከሚመለከተው ክፍል ጋር ሲነጋገር ከርሞ እኔና መክብብ ሰሞኑን ለፖሊስ ቃላችንን እንድንሰጥ ይዞን ሂዷል"፤ ብሎ እንብበ እንደጨረሰ "እ.. እ ቆይ፣ ትርሲት ይሆን ካለችኝ አይቀር ልጨምርበት" እለና "ታዲያስ ፍርዬ፣ ይኸኛው የእጅ ጽሁፍ ደግሞ የመክብብ ታምራት ነው እለና::

እንደምታስታውሽኝ ተስፋ አደርጋለሁ:: ትርሲትዬ ይሆን ደብዳቤ ከጻፈችልሽ በሁዋላ አንብበውና የረሳሁት ካለ ጨምርበታን ላክላት ነበር ያለችኝ:: በእርግጥ የረሳችው ምንም ነገር የለም:: ደብዳቤውን ከሰጠችን በሁዋላ ግን ፖሊስ ጣቢያ ሂደን ነበር:: እናም ዘውትር እንደምትለኝ ስበሳጭና ስደነግጥ ሆዴን በጣም ይቆርጠኛል:: እነዚያ አረመኔዎች ያስቃዩኝም



እስካሁን ስሜት አለኝ ትለኝ ነበር:: እናም ፖሊስ ጣቢያ ቃሏን እየሰጠች እያለች በጣም ታማብን በአስቸኳይ ሆስፒታል ወስደናት ሆስፒታል እንደደርስንም አቶ ነቢዩ ሳላጋንን ካሉት ሠራተኞች ከግማሽ በላይ ያውቃቸዋልና እስፈላጊው እንክብካቤና ህክምና ተደርጎላት ጽንሱ ተበላሽቶ እስ ግን ተርፋለች::

ምን ይደረግ እንግዲህ በእግዜር ሥራ ውስጥ መግባት አያስፈልግም:: ለማንኛውም ሰሞኑ ስለምትወጣ አቶ ነቢዩጋ ደውይ ወይም እኛ እንደውላለን::

በተረፈ ስለደህንነታችን ምንም አታስቢ:: ባይገርምሽ ገብረብሩክና አጫፋሪዎቹ በቁጥጥር ሥር እስከሚውሉ ጉዳት ሊያደርሱብን ይችላሉ ብሎ ፖሊስ በመጠርጠሩ በዐይነ ቁራ እየጠበቁን ነው:: እኛም የተቻለንን ያህል በግላችን እየተጠነቀቅን ነው:: ሽንኩሩ ውስጥ ያሉ ታቦቶች እን ሰሚዎች መሰሉሽ! ለአቡየ፣ ለመርቆሪዎስ፣ ለጊዮርጊስ፣ ለአማኑኤል፣ ለሚካኤል፣ ለመጥምቁ ዮሐንስ፣ ለክርስቶስ ስምራ፣ ለተክልዬ፣ ለዶፋው ሚካኤል..ምን ብዦ ልንገርሽ ያልተሳልኩላችሁ ታቦት የለም:: አይን ለአይን ቤተሰባችሁ ሁሉ እንዲተያይ ብዬ፤‹‹ ከቶ ለነሱ ምን ይሳናቸዋል››

ምን ጊዜም ያንቺው ወንድማችሁ መክብብ ታምራት ነኝ" ብሎ እሻሽጎ ላከና አካባቢውን እየቃኘ ጉዞውን ቀጠለ::

" የወንደላጤ ነገር፣ ባገኙበት መብላት ባገኙበት ማደር፣ ያዩትን ማሽኮርመም፣ እነአያ እንደልቡ ምን የማይባሉት አለ››? ይህ አይነቱ የወንደላጤ ባህርይ ገብሩይን ሲያልፍም

አይነካው:: የዕለት ተግባሩን ሲያከናውን ውሎ እራትን ቀማመሰ:: ጎኑን ለማሳረፍ ተቻኩሎ እቤት እንደደረሰ "ዘውዲቱ፣ አረ ዘውዲቱ ብሎ ቢጣራ" ምንም መልስ የለም:: ወቸው ጉድ ምነው ልጄ ሌላ ጊዜ ከዚህ የባሰ ሳመሽ እንኳን ጥላኝ ተኝታ አታውቅም:: የት ሄደች" ብሎ አሁንም ተሰፋ ባለመቁረጥ ደጋግሞ ተጣራ:: የድምጹ ጩኸት ከቤቱ በስተጀርባ ያለው የአንበሳ መድሃኒት ቤት ተረኛ መድሃኒት ቤት ቢሆን ኖሮ ወደጆቹ የአንበሳ መድሃኒት ቤት ሠራተኞች 'ምነው ገብሬ-ይ ምንድነው እንደዚህ የሚያሰጮህህ፣ ደህና አይደለህም ወይ?' ይሉት ነበር::

"እቤት ውስጥ የለችም ማለት ነው እንጅ እንዲህ ስጮህ እንኳን ከእንቅልፍ መቀስቀስ ቤትም ያነቃንቃል፡እስቲ ለማንኛውም ብሎ መኝታ ቤቷን ሲከፍት አንሶላና ብርድ ልብሷን ተከናንባ ለጥ ብላለች:: ገብሬ-ይ በጣም ተገርሞ 'ኃይለኛ ራስ ምታት አለብኝ' ትለው ስለነበር "ይይ ራስ ምታቷ ተነስቶባት ይሆናል፣ ቢሆንም..." እያለ አልዋጥልህ ብሎት ወዲያና ወዲህ ህይኑን ሲያንከራትት ወደ ውጭ የሚያስወጣው መስኮት ከእሷ መኝታ ቤት ጋር ተያይዘው አለመዘጋቱን አይቶ በመገረም "ሆሆይ አሁንስ አበዛችው፣ ሌቦች ወይም ድመቶች ገብተው ያስደነግጡኛል ብላ ፈርታ እንኳን መስኮቷን አትዘጋም እንዴ!" ብሎ እንደደንቡ ከውስጥ ቆለፈው::

የምግብ ጠረጴዛው ላይ ያገኘውን አንድ ሙዝ ገመጥ ገመጥ አድርጎ ውሃውን ጉንጭት ብሎ ወደመኝታ ቤት ገብቶ ልብሱን አወላልቆ ለመስቀል ቁምሳጥኑን ለመክፈት ቁልፍ አውጥቶ ሲጠጋ ቁም ሳጥኑ የተዘጋ መስሎ አልተቆለፈም



ነበር:: "ዛሬ የእኔም ልብ ጠፍቷል:: ጠዋት ሳልቆልፈው ሄጄ ኖሯል" ብሎ ክፍት ሲያደርገው ሁልጊዜ ቁምሳጥኑን በከፈተ ጊዜ እይኑ ውስጥ የሚገቡት የእጅ ቦምቦች፣ ሳይለንስር የተገጠመለት ሽጉጥ፣ በቦታቸው የሉም:: እያስቸገረው ያለው እንቅልፍ ክንፍ አውጥቶ በረረ፣ ክው ነው ያለው:: ያወለቃቸውን ልብሶች ከመቅጽፈት እንደገና ለባበሰና ወደ ዘውዲቱ ክፍል በመሄድ፤

ስሚ ዘውዲቱ ዛሬ እዚህ ቤት የመጣ ሰው ነበረ እንዴ ብሎ ነቅንቅ ነቅንቅ ሲያደርጋት ምንም መልስ በማጣቱ አንሶላዋን ገለጥ አድርጎ ጭንቅላቷን ነትንት ነቅንት ቢያደርጋትም ምንም አለመንቀሳቀሷ ገርሞት እየተርበተበተ "ዘውዲቱ፣ አንች ዘውዲቱ" ብሎ ክንዷን ነካ ነካ አድርጎ በድን መሆኗን ሲያውቅ "በስመ አብ" ብሎ እራሱን በመያዝ ቶሎ ብሎ ወደ ስልኩ እየሮጠ ቢጠብቅ ቢጠብቅ ቶን ማግኘት አቅቶት ሲመረምር ስልኩም ተበጣጥሷል:: ከመደንገጡ የተነሳ ሞባይል ስልክ እንዳለው የተረዳው የቤቱ ስልክ አለመሥራቱን ካወቀ በሁዋላ ነው:: ቤቱ በአጭር ጊዜ ተከበበ::ዘውዲቱም ወደ አባዲና፣ ፖሊሶችም እንደየሙያቸው የገብሬ-ይን ቤት ቁም ስቅሏን እያሳዩዋት ነው::

እንደሚታወቀው ባልቻ ሆስፒታል ጽንስን በማስወገድ ተወዳዳሪ የሌለው የረጅም ጊዜ ልምድ ያለው ሲሆን፣ ትርሲትም የዚህ አንጋፋ እዋራጅ (ማስወለድ) ሆስፒታል ተጠቃሚ በመሆኗ ደስ የሚያሰኝ ሆኖ አግኝታዋለች:: እድሜ ለነቢዩ ነገሮች ሁሉ ተቀላጥፈው በሚገባ ከተረዳች በሁዋላ ከሆስፒታል እንደወጣች ወደተዘጋጀላቸው ቦታ እንዲሄዱ

ሲነገሩቸው ወደ ሽንኮሩ ለመሄድ ቀደሃ" ብለው የያዙት እቅድ ስላላቸው እንደሚሄዱ ሲነግሩት ነቢዩ እንዳይሄዱ ለማስፈራራት የተጠቀመው ዘዴ "ምነው ልጄ እንዴት ከአዲስ አበባ ወደ ገጠር ይኬዳል ሲለው፡ መክብብ ጊዜም አልሰጠው፡ ይሉኝታም አላጠቃው፡ "እንዴ ላደለውማ አሁን ነው እንጅ በተለይ ወደሽንኮሩ መሄድ፡ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት ሕዝብ መሃከል ባይበሉም ባይጠጡም ወዲያ ወዲህ ማለቱና መንሸራሸሩ ራሱ ምግብ ነው። ሽንኮሩ እኮ ገጠር የምትለው አይደለም፡ አዲስ አበባ እንዲህ እየተለጠጠ ከሄደ ሽንኮሩ ደርሶ ያኔ መብራት በመብራት፡ ስልክ በስልክ ይሆንልናል።

ያጋጣሚ ነገር ሆነና ባጭሩ ተቀጨ እንጅ የመጀመሪያው የስልክ መስመር በሽንኮሩ በኩል ነበር የተዘረጋው ይባላል።

እንዲያው እቶ ነቢዩ ረሳኸው መሰለኝ እንጅ ሽንኮሩ ውስጥ ዘርተኸው የማይበቅል የእህል ዘር አይነት የለም። እየሩ በክረምትም በበጋም አንድ አይነት የሚለበስበት ነው። ምግቡም ሁልጊዜም አዳዲስ ወይም ፍሬሽ ነገር ነው የሚበላው። እንደምንለማው ትዮጵያ ውስጥ የገጠሩ ሕዝባችን የሚመገበው ምግብ በአውሮፓና በአሜሪካ አርጋኒክ ምግብ እያሉ በጣም በውድ ነው እሉ የሚሸጡት። ለነገሩ ፍሪጅ ውስጥ ያልዋለና ያላደረ፡ በመኪና ያልተንከራተተ እዚያው በዚያው እንጮ የተዘጋጀ፡ በተለይ የአትክልት ዘሮች ለጤና ጥሩ ናቸው ይባል የለ!

አይ ሽንኮሩ! የክፍተ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ከፍተኛ ክሊኒክ፡ የቧንቧ ውሃ፡ አሌክትሪክ ከተቻለ፡ ካልተቻለ እንዱ



እንኳ ቢኖረው እገሩስ አገር ነበር። ይቅርታ አቶ ነቢዩ በወሬ ጠመድኩህ።"

"እረግድ የለም፡ የተናገርከው በትዝታ ይዞኝ ጭልጥ እያለ ነው። አይዞህ የተመኘኸው ይሳካል። ለማንኛውም አንተም ትምህርትህን በርታ፤ እኔ በበኩሌ አንተን ካገኘሁ ጀምሮ በጣም ደጋግሜ ስለሽንኮሩ ብቻ ሳይሆን ከሽንኮሩ፡ ከምንጃር፡ የባሱ እልም ያሉ ገጠሮች ውሃ፡ ህክምና፡ ት/ቤት ፈጽሞ ስለሌላቸው ጭምር እያሰብኩ ነው።

የሚገርምህ እኔም እዚያው ሽንኮሩ ውስጥ በዓለም ላይ ዝናቸው የገነነው የቀድሞው ጠ/ሚ አቶ እክሊሉ ሃብተወልድ፡ ኤርትራ ከእናት አገሯ እንድትቀላቀል በዓለም አቀፍ ፍ/ቤት ተሟግተው ያሸነፉት፡ ሲሆኑ እኚህ ታላቅ ሰው የደርጎቹ ባለሥልጣናት ተብየዎች የተገደሉ፡ ዝነኛው አርበኛ ያንተው አያትና ብዙ ለአገራቸው አኩሪ ተግባር የፈጸሙት የተፈጠሩባት ሽንኮሩ የተባለች አገር መፈጠሬን ነግሬሃለሁ። ነገር ግን ደርግ የተባለ የነገውን የማያስብ ከትምህርታቸው ጉብዝና የተነሳ ራሳቸውንና አገራቸውን ወደከፍተኛ እድገት ይቀይራሉ የተባለላቸውን ተማሪዎች ከኢሕአፓ ጋር አብራችሁዋል እያሉ ስንቶቹን ፈጅቸው መሰለህ።

እንኳንስ ተማሪዎቹ እንደመንግሥት እንቀበልህም ያሉት ይቅሩና ለአገራቸው ለነጻነታቸው ስንት የወጡ የወረዱ አባውንቶች "እረ ተው ' ይህ የምትሠሩት ድርጊት ኢትዮጵያዊነት አይደለም፡ አሁን እናንተ ባለመሳሪያ ነን ብላችሁ በነዚህ ተማሪዎች ላይ የምታደርጉት ድርጊት ፋሽስት ኢጣሊያን በሕዝባችን ላይ ያደርግ ከነበረው ይበልጣል እንጅ

አያንስም፣ ተው፣ አምላክን ፍሩ በማስታቸው አዛውንቶችንም ይገድሉ ነበር:: ሽንኩራ ውስጥ ያልታሠረ ጉድ የለም:: ረጅሙ ሀልማቸው ባጭር የተቀጨው 'አይዞህ በርታ ጎበዝ' ይሉን የነበሩት በዘይት የተጠበሱት፣ ..ብቻ ስንቱ አለቀ!! ..ምኑ ቅጡ!! ለዚህ ነው ፊቱን ወደ ሽንኩራ ማዞር ሲዘገንነኝ የኖረው" ሊለው አሰበና "እ..እ..! የምን ነገር መቆስቆስ ነው" ብሎ "እንግዲህ መሄድ ካለባችሁ ሂዱ፣ በሰላም ያግባችሁ፣ እንደምንም ብላችሁ ቢያንስ በየሁለት ቀን ስልክ ደውሉልኝ" ብሎ ወደ ወንጀል ምርመራ በረረ::

እንደደረሰም የቀይ ዳማ አጥር ምጥን ሽንቀጥቀጥ ያለች ከየት መጣች ከየት ሳታስታውቅ ግድግዳ የሚመስል በር ገፋ ሲያደርጉት ከሚከፈት ውስጥ በድንገት ብቅ ብላ ጤና ይስጥልኝ አቶ ነቢዩ፣ ሂሩት እባላለሁ:: ዛሬ ወደዚህ የፈለግንዎት ሁላችንም እንደምናውቀው የሰሞኑ ሁኔታ ማለትም የነገብረብሩክ አሸባሪነት እየተስፋፋ መጥቷል:: እስካሁን ከገብረብሩክ በተተኮሰ ጥይት አንድ ሰው ሲሞት ይኸው ግለሰብ አንድ የቤት ሠራተኛንም አስገድዶ ከደፈራት በሁዋላ አንቆ ገድሏል:: ከዚህ ሰው ጋር አይጥና ድመት ሆነን ስለሆን ያለነው በቁጥጥር ሥር አስከምናውለው ድረስ ትርሲትን እየረዱት ያሉትን ብቻ ሳይሆን ከሷ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ይኖረዋል ብሎ የጠረጠረው ሰው ላይ ጉዳት ከማድረስ ስለማይመለስ ለእርስዎም ለአልተወሰነ ጊዜ ከርቀትም ሆነ ከቅርበት የሚጠብቅዎ ሃይል ልንመድብልዎ አስበን ነው የጠራንዎ:: በማንኛውም ሰአት ያላማርዎትን የሚጠራጥሩበት ነገር ሲያጋጥምዎ ደግሞ በነዚህ ቁጥሮች ይደውሉ::



ገብሬይ ሃዙን ዋጥ አድርጎ ሥራውን በመቀጠል የትርሲትን የተበላሸ ጽንስ ምርመራ ውጤትና ሌሎችንም መረጃዎች አሰባስቦ በማቅረብ ዋራንት አስወጥቶ ገብረብሩክን በተገኘበት በቁጥጥር ሥር ለማዋል አስፈላጊውን መሰናዶ ጨርሶ በየክፍለ ከተማው ኪላዎች ሳይቀሩ ፍተሻ በፍተሻ ቀውጢ ሆኗል:: እወ/ሮ አረጋሽ ቤትም አነጣጥሮ ተኳሾች በጥንቃቄ ጎረቤት እንኳ ሳያያቸው እቤት ውስጥ ገብተው ሌት ተቀን እየጠበቁ ነው:: እንዲያው ለምናልባቱ ወይ ወ/ሮ አረጋሽንን ለመተናኮል፣ አለበለዚያም በጣም የሚያስፈልገውን ነገር ለመውሰድ ድንገት ሲመጣ ካጋጠመን ብለው ነው እንጅ ከሠራቸው አጸያፊ ድርጊቶች አንጻር እንኳን እመኖሪያ ቤቱ ሊመጣ ቀርቶ ገርጅ አካባቢም ዝር የሚል አይመስልም::

ልክ ከምሽቱ 12 ሰዓት ብዙጊዜ ወ/ሮ አረጋሽ ከሥራ አቤቷ የምትገባበት ሰዓት ስለሆነ ስልኩ ብዙም ደጋግሞ ሳያንቃጭል ወ/ሮ አረጋሽ ማይክራፎን ላይ አድርጋ ሃሎ አለች:: ድምጹን ቀይሮ " ማን ልበል የእኔ እመቤት " ሲላት እሱ መሆኑን አውቃ አሷም እንዳላወቀች ሁና "አቤት ማን ብለው ደወሉ" ስትል ፖሊሶቹ ልክ ከውጭ የሚተላለፍ የፖሊቲካ ሬዲዮ ዛሬስ ምን አለ ምን ሊፈጠር ይሆን ብለው በመጓጓት የሚያዳምጡ ነው የሚመስለው:: የስልኩ ቀሮ ላይ ጭንቅላታቸው ገጥሞ ጆሯቸው ቀርቦ ላያቸው፣
"ምነው የኔ እመቤት አይቆጡ እንጅ፣ መሳሳት ያለ እኮ ነው::"
"አረ የኔ ጌታ አልተቆጣሁም !"
"እሽ ካልተቆጡ የት ነው የደወልኩት ታዲያ?"

ፖሊሱ በነጭ ወረቀት ላይ ጽፎ "የአቶ ገብረብሩክና የወ/ሮ አረጋሽ መኖሪያ" በይው ሲላት፣ ወ/ሮ አረጋሽም እንደተባለችው ስትል ፣

"አቶ ገብረብሩክ ወይም ባለቤታቸውን ላናግራቸው እችላለሁ?"

"አቶ ገብረብሩክ እንኳን ለጊዜው የሉም፣ እኔ ግን ባለቤቱ ነኝ"

"አ! ጤና ይስጥልኝ፣ በዝና ነው የማውቅሽ፣ አቶ ገብረብሩክን የማገኝበት ስልክ ይኖርሽ ይሆን?"

"የግል ስልክ ዝም ብሎ ለማንም ይሰጣል እንዴ? እርስዎን ለመሆኑ ማን ልበል?"

"አይቆጡ ብያለሁ እኮ፣ ሰውን የሚያክል ታላቅ ፍጡር ማንም አይባልም:: ቀጥለሽ በጥፊ ሳትይኝ ልዝጋልሽ መሰለኝ::"

የቻለውን ያህል የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ድምጹን ለመቀየር ሞክሯል:: ስልኩ ከተዘጋ በሁዋላ ፖሊሶች ወ/ሮ አረጋሽን በማድነቅ ወዲያውኑ ወደ ቴሌ ኮሚውኒኬሽን በመደወል በትዝታ ሞባይል መደወሉን አረጋገጡ::

ትዝታ የወ/ሮ አረጋሽ መበሳጨትና የመልኳ መቀያየር በቁንጅና የበላይነቷን ያረጋገጠላት ይመስል ለሚያውቃቸው ሰው ሁሉ "ይገርማል ያቺን የመሰለች ውብ እንዲህ ጥውልግልግ ስትል ወይ አረጋሽ! ዝም ብላ እኮ ነው ባልተጨበጠና ባልተረጋገጠ ነገር እራስን አስጨንቆ ከሰውነት ተራ ማውጣት፣ አሁን ማን ይሙት ገብረብሩክ ሴት አጥቶ ነው እንደልጅ የሚያያትን ልጅ አንቆ የሚደፍረው? 'የማይሆን ነገር...ለምን አትናገር' ነው የሚባለው? እንዲያ ዝም ብላ ዙሪያ



ጥምጥም ሂዳ እግዜርንም ከምታስቀይም ብታርፍ ይሻላታል:: የቃል ኪዳን ባሏን ሰበብ ፈልጋ ከቤት አባራ ቤት ንብረቱን ጠቅልላ ለመያዝ ፈልጋ ነው:: እንጅ አገር ምድሩ በገብረብሩክ ላይ የምታስወራው ሁሉ የፈጠራ እንደሆነ ተረድቶታል" እያለች ታንሸካካለች::

ሁኔታውን በሚገባ የተገነዘቡት የወ/ሮ አረጋሽ ወዳጆች ደግሞ ትዝታ የምትነዛው አሉባልታ ህይናቸው ሳይሆን ልባቸውን እያስለቀሰው ነው:: አንዳንዶቹም እንዴት ለገብረብሩክ አለሙያዋ ጥብቅና ልትቆምለት ቻለች፣ እሷም እነሱም እየተቆናፈሩ ነው::

# ምዕራፍ ስድስት

ትርሲትና መክብብ በጥዋት በራሪ ሞጆ ላይ እንደደረሱ የላንድሮቨሯ ረዳት ሸንኮራ የሞላ፣ ሸንኮራ ሸንኮራ ይላል:: ሮጠው ሲጠጉት ላንድሮቨሯ ሞልታለች::

መክብብ ወደሸንኮራ ያለውን የመጓጓዣ ሁኔታ ስለሚያውቅ ምንም አላስገረመውም:: ትርሲት ግን "እንዴ የቱ ጋ እንቀመጣለን፣ በሚቀጥለውእንሂድ ስትለው፣ ነይ ግድ የለሽም የሚቀጥለውም ያው ነው ብሎ እንደምንም ገባ አሏንም እግሩ ላይ አስቀመጣት:: "ሰው በሰው ላይ" ቢቃ እንዲህ ናቸው አብዛኛዎቹ የገጠር መጓጓዣዎችን ማየት ጥሩ ነው:: የገጠሩን ሕዝብ ህይወትም አይደለም እንዴ? አላትና መድረስ አይቀር ባልዕጨ ከተማ ተደረሰ::

ይኸውልሽ እንግዲህ ይህቺ ባልዕጪ ከተማ ትባላለች። ጥንት አንድ ውሃ የጠማቸው አባውንት እንዲቷን ከረጻ እባክሽ ውሃ አጠጪኝ ቢሏት ከረጻዋም ውሃ የለኝም በማለቷ አባውንቱ አዝነው "ባል ያሳጣሽ፡ ባልዕጪ" ብለው ረገሚት፡ በዚያም የዚህች ከተማ ስም ሆነ ይባላል። ይህቺ ከተማ ብዙ ወንጀል ተሠርቶባታል። በሆነ ባልሆነው ከሩቅ ቦታ ገበሬውን አሥረው ያመጡና በግርፋት ቁም ስቅሉን ሲያሳዩት ሚስቱ ወይም ዘመዶቹ በሬውን ሸጠው ካጎረሱለት፡ በሁዋላ ነው ምህረት ተደረገለት ተብሎ የሚለቀቀው።

"እምቢ አሻፈረኝ ደርግ ለተባለ የተማረን ሃይል በጅምላ ለሚጨፈጭፍ አልበገርም ብሎ የሚያምጸውን ደግሞ በአንጣጥሮ ተኳሾቻቸው ያስገድሉና ለገበያ ሰው በሚሰበሰብበት ቀን ሬሳውን ዘርረው 'ይህን ያያችሁ ትምህርት ይሁናችሁ፡ አርፋችሁ ካልተገዛችሁ የእናንተም እጣ ይኸው ነው፡ እያሉ ሕዝብን ያሸብሩባት የነበረች ከተማ ነች።"

ትርሲት በፈረስ ጋሪ ላይ ተቀምጣ ስለማታውቅ እንደወተት እየተናጡ ብዙም ሳይቆዩ በወራጅ ወንዙ አናት ላይ የተቆረቆረችው እራንቡተ ከተማ እንደደረሱ ትርሲት በድንገት "ውይ እንዴት ያምራል! በእውነት ሳላጋንን ትንሽ ባፍ አልፎ አልፎ ቢተከልባት በፖስት ካርድ ላይ ከምናየው የፈረንጅ ከተማ ምንም አይተናነስም" ስትለው "አይ የዚህን አካባቢ እንኳን ትልቁ አባባ እራሳቸው ከጣሊያን ወረራ ጀምሮ በዚህ አካባቢ ብዙ ታሪክ ስላላቸው ከእሳቸው እንደበት እንስማዋለን"

ገና ሲያዩት "እሰይ የእኔ ልጅ እሰይ እሰይ! ምነው የእኔ አንበሳ፡ ምነው ልጄ ጥሩ እኮ አልሰራህም ምን አስጨከነህ



ጥፍት እልም አልክብን እኮ! በእርግጥ ደህንነትህን ናዝሬት ለዘመዶችህ መደወልክን ሰምተናል። እኛም ከዚያ በሁዋላ ነው እንቅልፍ እንኳን በደንብ መተኛት የጀመርነው፡ ይሁን የኔ ጌታ እንኳን መጣህልን።

ደግሞ ይህች እመቤቴ ማርያም አመሳስልከኝ አትበለኝና እመቤቱን የመሰለች ማናት? እስቲ ተጫወች፡ ማነው ስምሽ?"

"መክብብ ፈጠን ብሎ ትርሲት ትባላለች፡ እንደእህቴ የማያት ጓደኛዬ ስትሆን አገር ላለጎበኛትና እናንተንም ላለተዋውቃት ነው ይዣት የመጣሁት"

"ጎሽ እንኳን መጣሽ፡ አገሩስ የሚታይ ነበረ። ይኸውልሽ እዚህ አገር ሁሉ ነገር ሞልቷል። እንደልባችን ነው፡ ነገር ግን ከፍ ያለ ት/ቤት ስለሌለ ልጆቻችን እኛ እያለንላቸው ት/ቤት ናሲጋ ይንከራተታሉ።

ለመሆኑ የትምህርትህ ነገር እንዴት ነው? ብድግ ብሎ ሒማቸውን በመሳም፡ "አባባ ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብቻ ለመማር ፈተናውን በደንብ አልፌያለሁ። እንደመርከርም፡ እንደመሸለልም ቃጣቸው። ደስታው የሚያደርጉትን አሳጣቸው። ድምጹ ጠፍቶ የነበረው ልጃቸው መጣ ብቻ ሳይሆን መክብብ በዲግሪ አልፎ ወደ ዩኒቨርሲቲ ሊገባ ነው የሚለው ዜና ከተማዋን ዳር እስከ ዳር አጥለቀለቀው። እቶ ገብሩ ቤት ሄዶ ለመደሰት፡ እሳቸውንም ለማስደሰት የአካባቢው ሰው ትንሽ ስበብ ነው የሚፈልገው።

አዝማሪው ማሲንቆውን፡ ጎረቤቱ ከቲካላውን፡ ጠላውን፡ ጠጁን፡ ቢራውን፡ ለስላሳውን እያግተለተለ በማምጣት የአቶ ገብሩን ቤት ሦስት ወር ሙሉ የተዘጋጁበት ድግስ አስመሰሉት።

ትርሲትና መክብብም ጭንቅላታቸው ላይ ክብድ ይላቸው የነበረው ሸክም መቅለሉ እስከሚታወቃቸው ላባቸውን እያንጠፈጠፉ ሲጨፍሩ፣ ሲስቁ፣ ሲጫወቱ አመሹ:: በተለይ ትርሲት የሰው ትህትና ደስታዋን እጥፍ ድርብ አድርጎታል:: አዝማሪውም ጠጁን ጎንጨት እያለ 'ንክም ንክም ንክም ...' እያለ የመስንቆውን ግርጌ በሌላኛው ቀጭ ቀጭ ሲያደርግ፡ "በላ ተቀበላ!" አሉት አቶ ገብሩ በድንገት::

"እኔስ መጣች ብዬ እመቤቴ ማርያም በሰው ተመስላ፣
ከቤቱ የመጣች ሽትርትር ብላ ለካስ ትርሲቴ ናት የመክብብ ወለላ!
እባክህ እምላኬ እድሜ ጨምርልኝ ሠርጓን እንድድበላ፣
እየተባባሉ ሁሉም ተጳከሙ::

ወ/ሮ አረጋሽ በጥዋት አቢርዋ ስትገባ ብዙ ጊዜ ከሌላ ክፍል መልእክት ሲመጣ የምታየው አይነት እንሽሎጥ ከጠረጴዛዋ ላይ በማግኘቷ ተቻኩላ ከፈተችው:: 'በህግ እስካልተፋታን ድረስ ውዷ ባለቤቴ ልበልሽ እንጅ' ይላል ደብዳቤው ገና ከመጀመሪያው:: "በስመ አብ" ብላ አማትባ እንደባለፈው በድንጋጤ እንዳትወድቅ የተቻላትን ያህል ተጠንቅቃ እየተንቀጠቀጠች ማንበቧን ቀጠለች:: "ምንም ባልተጨበጠና መረጃ በሌለው ነገር እንቺም ከጠላቶቹ ጋር አብረሽ ስሜን በማጥፋትም ሆነ እንደ ወንጀለኛ ሲያሳድዱኝ እንዳማትተባበሪያቸው ተስፋ አደርጋለሁ:: ለመሆኑ ሁለታችንም እኩል ደክመን ያጠራቀምነውን ገንዘብ ምን የተማመንሽበት ነገር ቢኖርሽ ወይም እንዴት ብትጠይኝ ነው



ገንዘብ ማውጣት እንዳልችል ያስከለከልሽኝ? በእርግጥ የጠየቅሁበት ንግድ ባንክ ሁሉ ቀዶ ይጣራ እስከሚሉት ነገሮችን ከማንዛዛት በስተቀር ፈጽሞ ገንዘብ መጠየቅ አትችልም ያለኝ የለም:: በአጭሩ ሳትውይ ሳታድሪ የምታድርጊውን አድርጊ:: እኔ በንጽህናዩ ነጻ እስክወጣና ምቀኞቼ እንደማይደርሱብኝ ዋስትና እስከሚሰጠኝ ከእነሱ የሚበልጥ እንጅ ያነሰ ችሎታ ስለሌለኝ እራሴን ጠብቄ ከነጻነት በሁዋላ ትጻራችንን በሰላም እንደምንቀጥል እንዳትጠራጠሪ:: ባይገርምሽ ባለፈው የማርያም ዕለት ልክ ከሥራ በምትገቢበት አካባቢ ከቤታችን ፊት ለፊት ካለው ቆሻሻ ገንዳ ውስጥ ሆኜ በሩን ዘበኛሽ ሲከፍትልሽ ቡትቶ ለብሼ በመለመኛ ከረጢቴ ውስጥ በቢንና ሽጉጤን አስቀምጬ፣ እንደ ባህታዊ ጸጉሬን አስረዝሜ ከዘራዬን እየተደገፍኩ አጎንብሼ ወደ በሩ ተጠግቼ ስለማርያም ራቴን ብዬ ስለምንሽ ለዚያ ለጠውላጋ ዘበኛሽ 'ደራ ጎሽ የኔ ጌታ' ከፖሊሶቹ ራት የተራረፈውንና ዳቦ ጨማምረህ ስጣቸው ስትይው ከመገረም አልፌ በመናደዴ ወንጀል ልሠራ ነበር፣ ነገር ግን በትእግስት ነጻነቴን ባገኝ ይሻላል ብዬ አልፌዋለሁ:: ፖሊሶች ደክሜ በሠራሁት ቤት ንብረቴ ይዝናኑበት፣ 'ጊዜ የሰጠው ቅል..' እንደሚባለው ነው:: ለመሆኑ ምን አይነት ዘበኛ ነው 'የኔ ጌታ' እየተባለ የሚታዘዘው? ለሁሉም እድሜውን ይስጠን:: እውነቱ ሁሉ ቀስ እያለ ይወጣል:: እንግዲህ ይህን ሁሉ የምዘረዝርልሽ የእኔን ጀብድ ወይም ችሎታ ለመናገር ሳይሆን እንችን መጉዳት ብፈልግ እኪሴ እንዳለ ንብረት ወይም በቁጥጥሬ ሥር እንዳለሽ እንድታውቂ ነው:: እኔን ለማስከፋት

ምንም አትጣሪ። ምክሬን የምትቀበይ ከሆነ እኔ የምልሽን ስሚ"።

ጽሁፉን ራቅ ጠጋ እያደረገች ደጋግማ አነበበችው። የራሱ የገብረብሩክ የእጅ ጽሁፍ ነው። ብዙ ደቂቃዎች እንዲ በትንሹ፣ አንዳንዴ በትልቁ አየተነፈሰች "ይህን ደብዳቤ ማን ሊያመጣው ቻለ? ዙሪያየ በሉ ሰዎች ታጥሯል ማለት ነው? አፍ! የቊንቀት የውጥረት ህይወት፣ አሁንስ መረረኝ፣ ነው ወይስ ከገብረብሩክ ምን ይሳነዋል ልበል? ለማኝ መስሎ እቤቴ ውስጥ ማን እንዳለና ምን እየተደረገ እንደሆነ በቀላሉ ያወቀ ሰውዬ አቢሮዬ ውስጥስ ከሌላ መሥሪያ ቤት ተልከ የመጣ መስሎ ደብዳቤውን አስቀምጦልኝ ሄዶ ከሆነስ? ምን ይታወቃል አብረን እንኖር የነበረ ጊዜ የቢሮየን ቁልፍ አባዝቶት ከሆነስ? የሚሆነውንና የሚመጣውን ከማየት በስተቀር ምን ባደርግ ይሻላል?" ብላ ምንም ሳታመናታ ስልኳን በማንሳት ወደ ገብራይ ደውላ አቢሮ መኖሩን ካረጋገጠች በሁዋላ ደብዳቤውን ከነፍሱ ፋክስ አደረገችለት።

ገብራይ አሱም ምንም ጊዜ ሳያጠፋ፣ በአጠገባቸው በጣም በቅርበት የገብረብሩክ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ በመጠርጠር ፈጣኑ አርምጃቸው ለሁሉም ባንኮች ፎቶውንና ስሙን ካስተላለፉ በሁዋላ የታገደውን ገንዘብም ለመልቀቅ ወሰኑ። ወ/ሮ አረጋሽም እንደተመከረችው "ብታገኘውም ባታገኘውም" ብላ ካስመረችበት በሁዋሮል "የባንኩን ነገር ሳስበው ትክክል አልሰራሁም። ደንግጩ ነው ያሳገድኩት፤ አሁን ግን አስለቅቄዋለሁ፤ አንተ እንዳሰብከው ሳይሆን እኔ ሁሌም



ያንተው ነኝ። እንዳልከው ሁሉንም በትእግስት እንጠብቅና ወደፊት ትዳራችንን በሰላም እንመራለን" ብላ የጻፈችውን ልክ እሱ የላከላትን ደብዳቤ ያገኘችበት ቦታ አስቀምጣ ቢሮዋን ቆልፋ ወጣች።

አቶ ገብሩ 'ኤርትራ' ከማለት 'ባህረ ነጋሽ' ማለት ነው የሚቀናቸው። "የሚገርም ነገር ነው፣ ለመሆኑ የአባትሽን ሁኔታ ትስሚያለሽ ታዲያ?" መልስ ሳይጠብቁ "ይገርምሻል የባህረ ነጋሽ ሰዎች በተለይ አንደጣሊያን አይነቱ ጠላት አገራችንን ለመውጋት ከመምጣቱ በፊት በጉልበትና በማታለል ቊምር ኢትዮጵያኖች ሳይሆኑ የራሱ ዘሮች እንደሆኑ በጥቅም አየደለላቸው ጥቂቶቹን አሳሳተ። ባህረ ነጋሽን የጦሩ ማከማቻ አድርጎ የቀረውን የኢትዮጵያ ክልል ጨፈጨፈ። በጥቅማጥቅም አታሏቸው አንዳንዶቹ እናት አገራቸውን ክደው ከጣሊያን ጋር ተሰልፈው ተዋግተውናል፣ ይገርማችሁዋል፣ ብዙዎቹ ደሞዛቸውን ጣሊያን ይከፍላቸዋል፣ የሚሰለፉት ግን ለእኛው ለእናት አገራቸው ለኢትዮጵያችን ነበር።

የባህረ ነጋሽ ክ/ሀገር ሰዎች በተለይ የሃማሴን አውራጃ ነዋሪዎች ጣሊያንን ለጥቅማጥቅም ሲሉ አብረው ቢሰለፉም፣ አርበኞች የመሸግንበትን ወይም የተደበቅንበትን ቦታ ሲያገኙት አጃቸውን በማወናጨፍ፣ ዞር በሉ አምልጡ፣ ዞር በሉ ይሉን ነበር። 'የእናንተ ጥቅም ባፍንጫዬ ይውጣ፣ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ እንጅ ምኔ ነውጣሊያናዊ የሚመስለው' ብለው በማመጽ ስንት ስመጥር የባህረ ነጋሽ አርበኞች ነበሩን መሰላችሁ። እኔ ከአባቴ ስለለመድኩት ባህረ ነጋሽ ነው ብዬ የምጠራው። እናንተ ደግሞ ጠላታችን ጣሊያን ባወጣላት ስም ኤርትራ ትሏታላችሁ።

ሰንደቅ ዓላማችንንም ልክ እንደጣሊያን ባንዴራ እያላችሁ በጣም ነው ቅር የሚያሰብለኝ::

ጊዜውም ስለረዘመ፣ የአካባቢውን ሰው እንዳልኳችሁ በሽሚዙም በሹሙቱም እየደለለ ኢትዮጵያዊ እንዳልሆነ እያስተማረ እየሰበከ የተከሰው መርዝ ይኸው ርቀን ሳንሄድ አባቴ 1885 ጣሊያን በጦርነት ሲነዋቀን አየ:: እኔ ልጁ ደግሞ እድሜ ለአከሊሉ ሃብተወልድ አይገብበብት ገብቶ አስመለሰልን:: ይኸው አይኔ እፍጥጦ እያየ እንደገና ተወሰደች::

"አባባ" አለ መከብብ በድንገት፤

"አቤት የኔ ልጅ!"

"ኤርትራ እኮ ማንም አልወሰዳትም፣ እራሷ ነች ነጻነቷን ያወጀቺው፣

"ነጻ ነው የወጣችው አልከን፤ በቃ ይኸ ነው የዘመኑ ልጆች፡ትምህርታቸሁ እንዴት ያለው ቀጣፊ አስተማሪ ነው እንዲህ ብሎ ያስተማረህ ልጄ! ለመሆኑ ከማን ነው ነጻ የሚወጡት? አየህ የኔ ልጅ፣ ነጻነቷን ተቀዳጀች(ቅኝ በኢትዮጵያ ትገዛ ነበር)የሚባለው እዚህ ምግብ ቤት እንደዚህ አይነት የሥራ ዘርፍ ላይ አይፈቀድላችሁም:: ባጭሩ ነጮቹ ሌሎቹን የአፍሪካ አገሮች ሲገዙ ያደርጉት የነበረውን አይነት አድርገንባቸው ቢሆን ኖሮ አዎን እውነትም ነጻነታችን አገኘን ቢሉ ሰሚ ሊያገኙ ይችሉ ነበር::

ለመሆኑ አምባሳደር ትላልቅ ነጋዴዎች፣ ባለሀንጻዎች፣ ባጭሩ



አለ አለ የተባለው ጥሩ ነገር በሙሉ በነሱቁጥጥር ስር አልነበረም? ይህን ሁኔታ መቸም ጤነኛ አእምሮ እንዴት እንደሚቀበለው ግር ይገባኛል::

አቶ ገብሩ መቸም እንዲ ጨዋታ ከጀመሩ ቀጭ ብሎ ማዳመጥ ያስፈልጋል:: ሽንት እንኳን ቢወጥር ቋጠር ያዝ አድርገው በእርግጥ ምግብ ባሰፈሰገ ጊዜ መብላት፣ ሲጠማም መጠጣት፣ መጸዳዳት ሲያስፈልግም ወዲያው መጸዳዳት፣ በመሠረቱ መሆንና መደረግ ያለበት ነገር ነው:: ነገር ግን ድንገት ችግር አጋጥሞ ከላይ የዘረዘርኩላችሁን ማከናወን የማይቻልበት ሁኔት ቢፈጠር ስሜትናን ሰውነትን ማለማመድ ያስፈልጋይል:: እያችሁ እኛ ፋሽስቱን ጣሊያን አምስት የመከራ ዓመት ስንዋጋው ረሃቡን ተውት የለመዳል፣ ባንዲት ባቄላም ይታደራል:: ውሃ ጥም ግን እንዴት ከባድ ነገር መሰላችሁ:: የራሳችንን ሽንት እየጠጣን ነው ተስፋ ሳንቆርጥ አዋርደን ያባረርነው:: ችግርን ባይችግርህም መለማመዱ ጥሩ ነው:: አንድ ቀን ችግር ቢያጋጥምህ ምድርና ሰማዩ የተደፋብህ እንዳይመስልህ" የሚለው የዘወትር ምክራቸው ነው::

"ከባእልጭ ወደዚህ ስትመጡ እንደሰፊ መንገድ አቋርጣችሁ የመጣችሁት ትዝ ይልሻል?፡

"አዎ ፡ አሰች ትርሲት:: ይኸውልሽ ልክ እሱ ጋ ብዙ ብረታብረቶች የወዳደቁ ሁሉ አሉ::"

"እ.. አይቻለሁ" እሱ ቦታ ማለት ጀኔራል ...ጀኔራል አባቴ ይጥፋና የእሱ መኖሪያ ቤት ነበረ:: ያ ብረታብረት ያየሽው ደግሞ ጣሊያን ጥሎት የሸሸው የመኪናቸው የምናምኑ ስብርባሪ ነው:: የሚገርም ብረት ነው::

ይህን ሁሉ ዘመን ወደ አፈር ሳይቀየር ባለፍኩ ባገደምኩ ቁጥር ዝም ብለን እንተያያለን። አፍ ቢኖረው ስንተ ግዜ ይቅርታ ባለኝ ነበር። ጆሮ ኖሮት ቢሰማኝም አንተ የምትገርም ጉድ ጉዳጉድ ለመዝረፍ ስትል ጥረው ግረው የሚኖሩ ሰዎችን ለመጨረስ መርዝ ተሸክመህ የመጣህ አካይስት ሁለቴም ሦስቴም ባሪያህ ልታደርገን ሞክረህ ያልተሳካልህ አፍረተ ቢስ አያልኩ አንገቱን አስደፋው ነበር።

ልክ ብረቱን ሳየው እድሜየን ሙሉ በተለይ ነፍስ ካወቅሁ ጀምሮ አባቴ የነገረኝንና እኔ የማውቀውን እየዳመርኩ በሃሳብ ጭልጥ አድርጎ ይወስደኛል። አንዳንዴማ ሳስበው ቆም እልና በከዘራዬ ገፋ ገፋ፣ ነካ ነካ አደርገዋለሁ። ምን ዋጋ አለው። አይናገር አይጋገር። እኔን በሃሳብ ጭልጥ አድርጎ ከመውሰድ በስተቀር። ብቻየን ስሆንና የሚያነጋግረኝ ሳጣ ቀስ እያልኩ አዘግምና አጠገቡ ቆም ስልገና እንዴት ያጫውተናል መሰላችሁ። ከፋሽስቱ ጣሊያን ጋር የተሠራረነው፣ ፋሽስቱ በግፍ የጨረሳቸው ወገኖቼ በማጭድና በመጥረቢያ የገዛ መሳሪያውን እየነጠቅን እንዴት አድርገን የዓለም መሳቂያ እንዳስደረግነው አወጣ አወርድና እንዴት ተንፈስ ብዬ እመለሳለሁ መሰላችሁ። አደራችሁን እኔ ስለፈልፍ እንዳታንቀላፉ፡"

"አረ አባባ ጥሩ ትምህርት ነው፡"

"አይ ጣሊያን ሞኝ እኮ ነው። አንዳንዴ ፖለቲካውንም ረጋ ብለው ካሰቡት ያን ያህል የበሰለ አይደለም። ገለባ ነበረ እኮ። ጥሩ ቢሆንማ ኖሮ መች እናምጽበት ነበር። አያችሁ ነጮች አፍሪካን ሲቀራመቱ ጣሊያንም ኢትዮጵያን ካለእኔ ማንም



አይወስዳትም ብሎ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ ደግሞ ደጋግሞ የሞከረው የእኛ የኦርቶዶክስ ሃይማኖታችን ከነሱው የካቶሊክ ሃይማኖት ጋር ይመሳሰላል ብሎ ስለገመተ ሕዝቡን በሃይማኖትም በምንም አታልዬ እገዛለሁ ብሎ ነበር። የሀልም እንጀራ ሆነበት እንጅ።ለአጉል ተራ ብልጥነት ካልሆነ በስተቀር የካቶሊክ እምነት ከኦርቶዶክስ ጋር ምን አገናኘውና! እነሱ ሮብና አርብን ሥጋና ቅቤያቸውን እየጠረገ ቅርጥፍ አድርገው እየበሉ እንዴት ከእኛ ጋር ይመሳሰላሉ? እንዲያው ሃይማኖታቸውን ስሙን ከጠራሁት አይቀር በጣሊያን ወረራ ጊዜ እኛን ለመጨፍጨፍ የተዘጋጀውን ቦምብ የካቶሊኩ የሮማው ጳጳስ ለድል ያብቃችሁ፣ ድል ተቀዳጁበት ብለው በመስቀላቸው ባርከውታል። ያ ቦምብ ነው እንግዲህ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ወገኖችንን የጨረሰው። እኔም በዛን ዘመን ከፋሽስቱ የምጠቀመውን ለመጠቀም እነሱውጋ ስመሳሰክ ተቀጥሬ ስለነበረ ‹‹መቼስ ሁሌ አይሞላም››ይባል የለ፤ ከጠላት እየደበቅሁ ያጠራቀምኩት ጥይት ከደበቅሁበት ተገኘቶብኝ፤የት ልትወስደው ነው? ለማን ልትሰጥ ነው? እያሉ እንዴት ቁም ስቅሌን አሳይተውኝ ነበር መሰላችሁ፤

"እሽ አባባ" ትላለች ትርሲት ታሪኩ እንደጣማት በሚገልጽ አይነት።

"ከዚያማ እንዴ፣ ከበርሚል ውስጥ ቆሻሻ ውሃ ይሞሉና ራቁቴን ይዘፈዝፉኛል፣ ከዚያ ያወጡና በጎማ ጀርባ ጀርባዬን ይቀጠቅጡኛል። ይህ ሁሉ ውርጅብኝ ሲወርድብኝ ቅንጣት ታህል ፍንጭ አልሰጠሁዋቸውም። ደግሜ ድጋግሜ

የምላቸው ነገር 'እኔ ጥይት ከየት እንደ‑መጣ እኔም እንደናንተ ገርሞኛል' ነበር የምለው::

በሽታ ይቀረጣቸውና ለንት ጊዜ ኖሮ ኖሮ ይህ ዱርዬ የመንግሥት፡ ሃይለማርያም የተባለ መንደር ምሥረታ ብሎ አውጆ ያኔ ነው ለታሪክ ሲታይ የኖረን የዋርካ ዛፍ የቆረጠው::

ሁለት ወር ሙሉ ዙሪያውን በአራት ቆርቆሮዎች የታጠረች፡ ስፋቷ አንድ ሜትር በአንድ ሜትር የሆነች መቆምና መቀመጥ እንጅ ለመተኛት ፈጽሞ የማትበቃ በዚያ ላይ ጣራ የላት፡ ደግነቱ ወቅቱ ክረምት አልነበረም፡ ብቻ ምን አለፋችሁ፡ ለልሳ የመከራ ቀኖች ካለፉ በሁዋላ ይህ ሁሉ ያደረገኝ አልበቃ ቦሎት ያካባቢውን ሰው ሁሉ ክጠራ በሁዋላ እዚያው እባፍ ላይ፡ ጭር ይበልበትና ጭር እንዳለች ዱሮ ጭንቅላቴን ወደታች አግሬን ወደላይ ሰቅሎ 'እያችሁ ጣሊያንን የከዳ የሚደርስበትን፡ እኛን በመክዳቱ እግዚአብሄር ነው የፈረደበት' እያለ ወገኖችን ሊሸነግል ሞክሮ ነበር የሆነው ሆኖ በእግዚአብሄር ታአምር ያን ሁሉ መከራ አሳልፌ ይኸው እዚህ ደርሼ ታምራትን ወልጄ እሱ ተገደለ፡ እኔ ይኸው ለታሪክ ተጎልቻለሁ::

እግዜር ደግሞ ጥሎ አልጣለኝም፡ ታምራት መክብብን አፍርቶልኝ ሄዷል" እያሉ ሲተክዙ አነጋገራቸው ወደ ሃዘን እየሄደ ስለሆነ በመፍራቱ፡ "እሽ አባባ እንዴት ተፈቱ ታዲያ?" "ምነው ልጄ እኔ ለንት ዘመን ሳረሳው አንተ ባጭር ጊዜ ረሳሃው እንዴ? እንዴ ሳይሆን ባዙ ጊዜ አጫውቸሃለሁ እኮ የኔ ልጅ::"

"አይ አኔማ አረሳሁትም እኮ አባባ፡ ለትርሲትየ እንዲያጫውቷት ብየ ነው"::



"እእ.. የተፈታሁትማ ያ ቀዥቃዣ አስተርጓሚው አዲስ ጨርቅ ተለጥቶት እራቅ ወዳለ ቦታ ሱሪ ሊያስፋ ሊሄድ ሲል እኔንም ያን የማይለቋቸውን "ጥይቱን ከኛ ሰርቀህ ለማን ልትሰጥ ነበር?" የሚለውን ጥያቄአቸውን ሊጠይቁኝ እዚያው አካባቢ ስለነበርኩ እሩቅ መንገድ ከምትሄድ እኔ ልሰፋልህ አልኩ፤ አዛዦቹ ሁሉ ተስማሙ ተጨንቄ ተጠብቤ ሰፋሁለት ረጅም ተነፋነፍ ሲለብስ የመጀመሪያውም ስለስለነበረ በጣም ተደስቶ ታስሬ ውላ እንደተፈታች ጥጃ እሮጦ ፊነደቀ የምድሪ ሰላቶን ጫማ ሳመ እኔም ላይ ተጠመጠመብኝ፤

ይገርማል የባህሪ ነጋሽ ሰዎችን እኮ ጣሊያን ክፉኛ ነው ያታለላቸው አንዳዶቹ በጣሊያን ሳያመልኩበት ይቀሩ ይሆን? እና ይህውላችሁ በተነፋነፍ ሱሪ ተደስተው ወዲያውኑ ፈቱኝ እላችኋለሁ::

እኔም አመች ጊዜ እስከማገኝ ድምጼን አጥፍቼ ከነሱ ጋር ዋል አደር አልኩና በገዛ መሳሪያቸው አንድ ሁለቱን ኮርኩም አድርጌ ከአርበኞች ጓደኞቼ ጋር ተደባለቅሁ:: ከዛም ብዙ ሳንቆይ እኛ እየተጠናከርን ፋሽስቱ እየተዳከመ በጎጃም መስመርም እነበላይ ዘለቀ መውጭያ መግቢያ እንዳሳጡት ተባራሪ ወሬ እንሰማ ነበር እኛም ከዚህ እንዲሁ እያንበገበግነው ባጭር ጊዜ ውስጥ ከአገራችን ድራሹን አጠፋነው::

መቸስ የድምጽ ማጉያ እና መቅጃ አለመያዟ ነው እንጅ ትርሲት የምትጠይቃቸውን ጥያቄዎች ለንት ሰልጠና ያላቸው የቢቢሲ እና የሲኤን ኤን ጋዜጤኞችን ታስንቃለች:: "ይህንን ሁሉ ላገራችን አድርገው እንዴት ነው መንግስት አሁን እንዲህ ሊደክሙ ህክምናና የመሳሰሉትን ይረዳዎታል?"

"አይ የኔ ልጅ አሉን ተይውና አውቶብስ ለመሳፈር እንኳን ጉልበተኛው እየሮጠ ገፍቶን ሲሳፈር ለኛ ቅድሚያ እንዲኖረን ባደረጉልን ጥሩ ነበር፤ ወይ ህክምና! አንቺ ሀሳብሽ ትልቅ ነው፤ ጎሽ የኔ ልጅ ትልቅ ያድርግሽ።"

"ጡረታስ አለዎትን?"

"መች የመንግስት ስራ ሰራሁና፤ ያ ለነፃነታችን የታገልኩት ከሆነ፤ እሱ በእርግጥ ሽልማትና ማዕረግ ያሰጣል፤ ቋሚ ደሞዝ ግን ከስንት አንድ ናቸው ለስበብ ስራ እየተሳጣቸው የሚከፈሉት የነበሩት።"

"እርሰዎ ምን ሽልማትና ማዕረግ አገኙ ታዲያ?"

"ሽልማቴማ መንከራተት፤ ማዕረጌ ያው አቶ ነው።"

"እንዴት?" አለች ተቻኩላ።

"ያው እንግዲህ ስምታችሁ ከሆነ ኃይለ ሥላሴ ቀመኛ ናቸው፤ ያኔ ከሸሹበት ከእንግሊዝ አገር ከድል በኋላ በየክፍላተ ሃገሩ እነ በላይ ዘለቀን ጨምሮ የት እናውቃቸዋለን፡ እንዴት ያልደከሙበትን ብለን ትንሽ አጉረምርመን ይሽ ባንዳው ምናምኑ እኛን ለጣሊያን እየጠቆመ ሲጠቀምብን የኖረው ሁሉ "ፀሃዩ ንጉሳችን እንኳን በሰላም ወደ ሃገርዎ ተመለሱ" ብሎ ያውም ሰንደቅ አላማችንን ሳይሆን ነጭ ጨርቅይ አውብልቦ በመቀበሉ፡ ደጃዝማችነቱን ቀኛዝማችነቱን፡.. ብቻ ምን አደከመሽ ሹመት በሹመት ሆነ። በእርግጥ ብዙዎቹ የእውነት አርበኞቹ የጃንሆይን ወደ አገር መመለስ በፀጋ የተቀበሉት የተመኙትን አይነት ሹመት ሁሉ ተሾመዋል። እየሽ እኔና ጓደኞቼ ግን ብልጠት ጎድሎን ሳይሆን ዋሽቶ ቀላምዶ ሹመት ለመሰጠት፡ በማይገባው ሰው ከመሾም ይቅርብን ብለን ጓደቼም



እንዳከረፉ ሞቱ፤ እኔ ግን "ትልቅ ሰው ይናደዳል እንጂ አያኮርፍም" እንደሚባለው ይኸው እንዳለሁ አለሁ። አሁን ደግሞ ምን አለብኝ ይኸው መክብብም እየደረሰልኝ ነው። በደህና ጊዜ ሠርቸ ያጠራክምኩትም እስከ እለቴ ሞቴ አንቀባሮ ያኖረኛል ብየም እገምታለሁ" እያሏቸው ሳለ በድንገት ሃሳባቸውን ለውጥ አድርገው "ለመሆኑ ያን ወሮበላ አጎትህን ታገኘዋለህ?" አሉ።

"አይ አባባ፡ ኸረ እኔ ባየውም አላውቀውም።"

"እንዴ! አባባ ሌላም ልጅ አሰዎት እንዴ?"

"ልጅ አልሽው፤ የእንግዴ ልጅ፤ እንዴው መልኩ እኔን ስለሚመስል ነው እንጂ ኪዚያ በስተቀር ምንም ነገር ከኔ የለውም። ብታይው ወረኛ፤ ውሸታም፤ እንዴው ለምሳሌ ያክል እግዚአብሔር አያድርግብሽና ዘመድሽ ሆኖ ቸገር ብሎሽ አንድ ሁለት ወር ከቤቱ ብትቀመጭ ባጭር ጊዜ ውስጥ ያሳደኳት ልጅ ብሎ በጥሩንባ ነው የሚያስነግረው። ማጋነን ይወዳል። እንዴት ያለው ምላጭ መሰለሽ ለአንድ ለሁስት ቀን ብቻ ከሆነ ያወቀሽው ደግሞ እየዲያ..፤ እንደዚህ አይነት ደግ ገራገር ሰው አንድ ሃምሳ እና ስልሳ አገራችን ቢኖራት ኖሮ እንድም ሰው ሳይራብ ያለውን ተቃምሶ ተዛዝ ኖ ይኖር ነበር ያሰብላል። ወረኛ ነው፤ ደግሞኮ ወጉ አልቀረበትም ከታምራት ጋር ኢሕአፓ ነኝ ብሎ አብሮ ያቸፈችፍ ነበር። ወንድሙንም ያስገደለው እሱው ሳይሆን አይቀርም በየቦታው ሲቀደድ፤ ብታይው ወንፊት ነው። ለነገሩ ኢሕአፓዎቹም ያስቀት አልቀው የተረፉትም ለአውሮፓና ለአሚሪካ ሲሳይ የሆኑት እንደሱ አይነት ልፍስፍሱን ሁሉ በማግበስበሳቸው

"አይ የኔ ልጅ አሱን ተይውና አውቶብስ ለመሳፈር እንኳን ጉልበተኛው እየሮጠ ገፍቶን ሲሳፈር ለኛ ቅድሚያ እንዲኖረን ባደረጉልን ጥሩ ነበር፤ ወይ ህክምና! አንች ሀሳብሽ ትልቅ ነው፤ ጎሽ የኔ ልጅ ትልቅ ያድርግሽ።"
"ጡረታስ አለዎትን?"
"መች የመንግስት ስራ ሰራሁና፤ ያ ለነፃነታችን የታገልኩት ከሆነ፤ እሱ በእርግጥ ሽልማትና ማዕረግ ያስጣል፤ ቋሚ ደሞዝ ግን ከስንት አንድ ናቸው ለስበብ ስራ እየተሳጣቸው የሚከፈሉት የነበሩት።"
"እርስዎ ምን ሽልማትና ማዕረግ አገኙ ታዲያ?"
"ሽልማቴማ መንከራተት፤ ማዕረጌ ያው አቶ ነው።"
"እንዴት?" አለች ተቻኩላ።
"ያው እንግዲህ ስምታችሁ ከሆነ ኃይለ ሥላሴ ቂመኛ ናቸው፤ ያኔ ከሸሹበት ከእንግሊዝ አገር ከድል በኋላ በየከፍላተ ሃገሩ እና በላይ ዘለቀን ጨምሮ የት እናውቃቸዋለን፤ እንዴት ያልደከሙበትን ብለን ትንሽ አጉረምርመን ይኽ ባንዳው ምናምኑ እኛን ለጣሊያን እየጠቆመ ሲጠቀምብን የኖረው ሁሉ "ፀሃዩ ንጉሳችን እንኳን በሰላም ወደ ሃገርዎ ተመለሱ" ብሎ ያውም ስንደቅ አላማችንን ሳይሆን ነጭ ጨርቅይ አውብልቦ በመቀበሉ፤ ደጀዝማችነቱን ቀኛዝማችነቱን፤.. ብቻ ምን አደከመሽ ሹመት በሹመት ሆነ። በእርግጥ ብዙዎቹ የእውነት አርበኞቹ የጃንሆይን ወደ አገር መመለስ በፀጋ የተቀበሉት የተመኙትን አይነት ሹመት ሁሉ ተሾመዋል። እየሽ እኔና ጓደኞቼ ግን ብልጠት ጎድሎን ሳይሆን ዋሽቶ ቀላምዶ ሹመት ለመስጠት፤ በማይገባው ሰው ከመሾም ይቅርብን ብለን ጓደቼም



እንጻከረፉ ሞቱ፤ እኔ ግን "ትልቅ ሰው ይናደጻል እንጂ አያኮርፍም" እንደሚባለው ይኸው እንጻለሁ አለሁ። አሁን ደግሞ ምን አለብኝ ይኸው መከብብም እየደረሰልኝ ነው። በደህና ጊዜ ሠርቶ ያጠራቀምኩትም እስከ እለቴ ሞቴ አንቀባሮ ያኖረኛል ብየም እገምታለሁ" እያሏቸው ሳለ በድንገት ሃሳባቸውን ለውጥ አድርገው "ለመሆኑ ያን ወሮበላ አጎትህን ታገኘዋለህ?" አሉ።
"አይ አባባ፤ ኧረ እኔ ባየውም አላውቀውም።"
"እንዴ! አባባ ሌላም ልጅ አለዎት እንዴ?"
"ልጅ አልሽው፤ የእንግዴ ልጅ፤ እንዴው መልኩ እኔን ስለሚመስል ነው እንጂ ኪዚያ በስተቀር ምንም ነገር ከኔ የለውም። ብታይው ወረኛ፤ ውሽታም፤ እንዴው ለምሳሌ ያክል እግዚአብሔር አያድርግብሽና ዘመድሽ ሆኖ ችገር ብሎሽ አንድ ሁለት ወር ከቤቱ ብትቀመጭ ባጭር ጊዜ ውስጥ ያሳደኳት ልጅ ብሎ በጥሩንባ ነው የሚያስነግረው። ማጋነን ይወዳል። እንዴት ያለው ምላጭ መሰለሽ ለአንድ ለሁለት ቀን ብቻ ከሆነ ያወቅሽው ደግሞ አየዲያ..፤ እንደዚህ አይነት ደግ ገራገር ሰው አንድ ሃምሳ እና ስልሳ አገራችን ቢኖራት ኖሮ አንድም ሰው ሳይራብ ያለውን ተቃምሶ ተዛዝ ኖ ይኖር ነበር ያስብላል። ወረኛ ነው፤ ደግሞኮ ወጉ አልቀረበትም ከታምራት ጋር ኢሕአፓ ነኝ ብሎ አብሮ ያቸፈችፍ ነበር። ወንድሙንም ያስገደለው እሱው ሳይሆን አይቀርም በየቦታው ሲቀደድ፤ ብታይው ወንፊት ነው። ለነገሩ ኢሕአፓዎቹም ያለቁት አልቀው የተረፉትም ለአውሮፓና ለአሚሪካ ሲሳይ የሆኑት እንደሱ አይነት ልፍስፍሱን ሁሉ በማግበስበሳቸው

አይደለም፡፡ከሁሉም የቆጨኝ ግን ያኔ በዚሁ በኢሕአፓ ሰበብ የታሰረ ጊዜ ያለ የሌለ ንብረቴን ሽጬ እሱን ጉቦ ከፍዬ ማስወጣቴ ነው፡፡

አደራሽን እናትና አባትሽን ጠይቂ ገንዘብ መስጠት ብቻ አይደለም መጠየቅ፣ እንደዚህ እኔን እንደምታጫውቱኝ አጠገብ ላጠገብ ተቀምጦ ዐይን ላይን እየተያዩ መጫወት እንዴት መንፈይስ ያድላል መሰላችሁ፤"

"እኔ የምለው" አለ መክብብ በድንገት፤ "እቤት ልጄ" አሉት፡፡ "አባቴን አጎቴ ነው ያስገደለው ማለት ነው እንዴ?" አቶ ገብሩ "አይ ልጄ!" አሉ፣ እንባ እየተናነቃቸው፡፡ "ግና ከአፌ ሲወጣ እኔም ፈርቼ ነበር፡፡

ምን ይደረግ እንግዲህ 'የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም' አይደለም የሚባለው? ይሁን አንዴ እምልጧል፡፡ እየሀ ልጄ ያን ያልኩት የአጎትህን ዝርክርክነት፣ ገለባነት፣ ሂትለርነት ለመጥቀስ ብዬ ነው፡፡ በዚያን ዘመን አባትህና ጓደኞቹ ያለቁበት ዓመታት በእርግጥ ወንድሙን፣ ጓደኛውን፤፤ እናቱን አባቱን ያላስገረፈ ያላስገደለ በጣም ጥቂት ሰው ብቻ ነበር፡፡ ሰንቱ ጎበዝ ተማሪ አስተማሪ፣ መሃንዲስ፣ ሃኪም ኢትዮጵያን ከፈረንጅ አገር ሊያስበልጡ የሚችሉ የነበሩ ኢሕአፓ፣ ሻዕቢያ፣ ወያኔ፣ ...እየተባሉ ሰንቶቹ አለቁ፡፡ በጥላቻ በጥቅም ለመሾም በፍርሃት፤ ብቻ ሰው ለመግደል ወይም ለማስገደል ቀላል ነበር፡፡

እንዲህ አድርጎ መጨካከን ምችም በዚች በተቀደሰች ምድር ያን ሁሉ ጉድ ማየት እስካሁን ሳሰበው ይዘገንነኛል፡፡ ከሁሉ የሚገርመው እስቲ ቆይ፣ ሽማግሌ፣ እዛውንት



ሊያጸምጡና ሊያከብሩ ይችላሉ ብለን ከእኔ ጭምር አሁን በህይወት የሌሉ አምስት እርበኞች ጓደኞቼን እስከትዬ ማመልከቻችንን ፈርመን ለኤረርና ከረዩ አውራጃ አስተዳዳሪ በእጁ ብንሰጠው፣ ግና ደብዳቤውን እንብቦ ሳይጨርስ በደወል ፖሊስ ጠርቶ የፊጥኝ ታሥረን ከሌባው፣ ከቀማኛው ጋር እሥር ቤት ወረወረን፡፡

"ውይ ምነው አባባ፣ ይህንንስ ነግረውኝም አያውቁ፣ ለመሆኑ ምን ጽፋችሁ ብታናድዱት ነው?"

"አዬ ልጄ፣ 'ሰንት እለ በሆዱ' ነው ያለችው ሴትየዋ? ሰንቱን ልንገርህ ልጄ! ይህን ሁሉ ዘመን ስኖር ሰንት አስገራሚ፣ እሳዛኝ፣ አስቂኝ ...ገጠመኞች አሉኝ፡፡

ህይወት ራሱ ውጣ ውረድ ብዙ ነገር እኮ ነው፡፡ያጨካኝ የመንግሥቱ ሃይለማርያም እሽከርማ ቢሰማን ቢያከብረን ብለን 'ለተከበሩት አስተዳዳሪ' እያልን ክበን ክበን፣ እባካችሁን የተማረን ሰው አትግደሉ፣ አብዛኛዎቹ ለእናንተ እንገዛም ያሉት ተማሪዎች በእድሜያቸውም ገና ወጣቶች ስለሆኑ'ጊዜ ስጧቸው፣ የሚሉትንም በትእግስት እዳምጧቸው፣ ጣሊያን የጨረሰን እንሶ እንዴት እርስ በርሳችን እንጨራረስ? ምነው እንዱ እሳት ሲሆን ሌላው ውሃ ሆኖ ማብረድ መስማማት ይቻላል፣ ለሁላችሁም ፍሬ እይሰጥም፣ ሁዋላ የፉክክር በረት ሳይዘጋ ያድራል እንደተባለው እንዳይሆንባችሁ' ብለን በመጻፋችን ነው!" ሲሉ ትርሲት ሳይሰሟት ለመክብብ፤ "እዎ እኑ እባባ ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ተጠቅመው ኖሯላ!" ስትለው፣ መክብብ ጮክ በማለት "አይ! ትርሲትዬ እንዳነበብኩትና እንደሰማሁት እንኳንስ እገራችን፣ እንኳንስ

እፍሪካ፣ ላቴን ኤሽያ ቀርቶ፣ አድገናል ተመንድገናል፣ ከማንም በላይ ሰልጥነናል የሚሉት አውሮፓና አሜሪካም ውስጥ የእውነት ወይም ትክክለኛ ዴሞክራሲ የለም።"

"ምነው ልጆቼ እኔን እመሃል ቁጭ አድርጋችሁ ጨዋታችንን ወዴት ወዴት ወሰዳችሁት?" ፈገግ ፈገግ እሉና "እንዴት ተፈታችሁ ታዲያ?" አለ።

"የምንጃርና የሸንኮራ ሕዝብ ለችግር ደራሽ መሆኑን መቸስ አገር ያውቀዋል። ሕዝቡን ክብር ምስጋና ይግባውና፣ ውስጥ ውስጡን ተመካክሮ ከፍሎልን ይቅርታ ተደርጎላችሁዋል ተብሎ ከአሰራ ሦስት ቀን ስቃይ በሁዋላ ለቀቁን።"

"ሁለተኛ አይለምደንም ብላችሁ?" አለ እየቀለደ። "ኧረ ወዴት ወዴት! የነሱማ ተንኮል ሌላ ነበረች። የፈረምነው ይል የነበረውማ 'በእናርኪስቶች፣ በአገር ገንጣዮች እና አስገንጣዮች ላይ መንግሥት እየወሰደ ያለውን እርምጃ ወደሌላ በመተርጎም መንግሥትን ከሕዝብ ጋር ለማጋጨትየሚያደርጉትን ሴራ መንግሥት ቢደርስበትም የሚመለከተው ክፍል ጉዳዩን በጥልቀት ከመረመረው በሁዋላ ምህረት አድርጎላቸዋል' ይልና ወደ መጨረሻው ደግሞ ማስፈራሪያም ነበረው። ያው ብቻ እንዳልኳችሁ ፈርመን ወጣን እላችሁዋለሁ። ተውኝ ልጆቼ አትንካኩኝ እባካችሁ። 'ሁሉንም ሆድ ይፍጀው'" እሉና ጸጥ ተባባሉ።

# ምዕራፍ ሰባት



ፒያስ ከመብራት ሃይል ፊት ለፊት ያለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንደወትሮው ትርምስምስ ብሎ ሠራተኞች ሙያዊ ብቃታቸውን ለመወጣት እነሱም እየተራወጡ ነው። ገብረብሩክ ይህን ባንክ ከመረጠበት ብዙ ምክንያቶች በጥቂቱ ለማምለጥ ከአራት በላይ አቅጣጫ ስላለው ሲሆን፣ እቅዱን ሲነድፍም ወደላይ ከሮጠ እጥፍ ብሎ ዶሮ ማነቂያ ክገባ፣ ወደታች ሮጠ ሠራተኛ ሮሠፈር ወይም መረባ ጠጅ ቤት አካባቢ ከደረሰ አላማው እንደሚሳካለት በመተማመኑሲሆን፣ ሌላውና ተቀዳሚ አላማው ደግሞ የሚፈልገኝም ጠላት ካለ ይመጣል ብሎ የሚጠብቀኝ ጭርና ጸጥ ያለበት አካባቢ ያለን ባንክ ነው እንጅ እንዲህ ትርምስምስ ያለ ቦታ ደፍሮ ይመጣል ብለው ስለማይገምቱ ብሎ በማሰቡ ነው።

ገና ፍተሻውን አልፎ እንደገባ ከሠራተኞቹ አንዷ ሞቅናደመቅ ያለ ሰላምታ ከሰጠችው በሁዋላ ጉዳይ ወደ ሚፈጽምለት ቦታ መራችውና እንደተጠጋ መታወቂያውን ገና ሲሰጠው የባንኩ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ስሙን እንብቦ መታወቂያውን ከፊት ለፊቱ በማስቀመጥ ስሙንም ፎቶውንም እፍጥጦ እያየ "ምን ልርዳዎት?" ሲለው "ባለፈው ጊዜ ብር ለማውጣት ብዬ ታግዶ ነበር። መለቀቁን ለማረጋገጥ ፈልጌ ነው።"

"ይታገሱኝ" ብሎ ከበስተሁዋላ ያለው ክፍል ውስጥ ገብቶ ብዙም ሳይቆይ ፋይል ይዞ ተመለሰና ከፊት ለፊት ቁጭ ብሎ ወ/ሮ አረጋሽ ምንዎ ናቸው? ሲል ላቀረበለት ጥያቄ "ባለቤቴ፣ የስማኒያ ሚስቴ ናት" ሲል መለሰ።

"አሁን አብራችሁ ነው የምትኖሩት?"

"ስማ ወንድም የዛሬዎቹ የባንክ ሠራተኞች ደግሞ ብር ቆጠራ ትታችሁ የሰውን የህይወት ታሪክ መመርመር ገባችሁ እንዴ?"

"ይቅርታ እኔ እንኳን እጠያየቁ እንዲያናድድዎት ብዬ ሳይሆን ባለፈው ጊዜ ታግዶ የነበረው በባለቤትዎ ትእዛዝ ሲሆን፣ አሁንም ብር ማውጣት እንዲችሉ የፈቀዱልዎት እሳቸው ስለሆኑ በዚህ ዙሪያ ወደፊትም ችግር እንዳይገጥምዎ ላማክርዎት ፈልጌ ነው።"

"ስለሃሳብህ በጣም እመሰግናለሁ:: አሁን ካለኝ የጊዜ እጥረት አንጻር ገንዘቤን ማውጣትና ማስገባት እችላለሁአልችልም ነው ጥያቄዬ፤ "

"በሚገባ እንደፈለጉት ማንቀሳቀስ ይችላሉ።"

"ይህን ለማወቅ ነበር፣ በጣም እመሰግናለሁ" ብሎ ብድግ አለና ዞር ሲል፤

ወደ ባንኩ ውስጥ ሰው እንዳይገባ ከውስጥ ያሉትም እንዳይወጡ በመታገዱ እራዳ የባሰ ቀውጢ ሆኗ ትርምስምሷ ወጥቷል:: ወደ በሩ ጠጋ አለና ለመውጣት ለጥበቃዎቹ ጥያቄ አቅርቦ የእንቢታ መልስ በማግኘቱ፣ እየተነጫነጨ እንደልመናም እየቃጣው ነው::

"እረ እባካችሁ ሀጻን ልጅ እቤት ነው ጥዬ የመጣሁት፤ ሃይለኛ የሲጋራ ሱስ አለብኝ፤ በሰዓት የምወስደው መድሃኒት አለኝ፤ ...እየተመላለሰ የማይደረድረው ምክንያት የለም:: እጉል መንቀዥቀዡ ያላማረው ጥበቃ ሰልችት ብሎበት "ስማ የእኔ ወንድም ምናለ ትእግስት ቢኖርህ? ይህ ሁኔታ እኮ ላንተ ብቻ የተደረገ አይደለም:: ከዚህ ሁሉ ሰው አንተን ብቻ ለይተን የምንጠቅምበት፣ የምንጎዳበት ምክንያት እንደሌለን አውቀህ



እባክህ ልቀቁ እስክምንባል በትእግስት ጠብቀን" እያሉት ሳለ ሲቪል የለበሱ መታወቂያቸውን ብልጭ ብልጭ አድርገው ገቡና እንደነብር ዘለው አንዱ ከሁዋላ አንዱ ከፊት ከታች አንስተው አፈረጡትና እጁን ጠምዘዘው ወደ ሁዋላ ካሠሩት በሁዋላ "አይ አሸባሪው ገብረብሩክ ለዚሁ ኖሯል ውኒጥ ውኒጥ ስትል የኖርከው?" አሉና እጆቹን ግራና ቀኝ ይዘው መኪናቸው ውስጥ ከሁዋላ አስቀምጠው ይዘውት በረሩ::

ገብራይ ገና ገብረብሩክ ወደጣቢያ ሳይደርስ የምስራቹን ለወ/ሮ አረጋሽ ነግሯት እቢሮዋ ቁጭ ብላ የማትጠራው የታቦት ስም የለም:: "እሰይ የኔ ጌታ፤ ካላንተ ማን አለኝ፤ እዎ በቃሽ በለኝ፤ እንደ ሰው እንቅልፍ እንኳ ጠግቤ ልተኛ እንጅ ዛሬ ነገ ገደለኝ እያልኩ እኔም ተጨንቄ፤ እምላኬ ሆይ አንተንም አስጨነቅሁህ፤ በቃሽ በለኝ" ትላለች:: ብዙም ሳትቆይ ስልክ ተብላ ስታነሳው ገብራይ ነበር:: የሚላትን ሳትሰማ፣ "ይኸውልህ የኔ ወንድም የእግዚአብሄር ታእምር ብዙ ነው" ብላ ገና ሳትጨርስ "እንዴ እዳምጪኝ ወ/ሮ አረጋሽ፣ ይኸ አካይስት ባልሽ ዛሬ በኛ ላይ ትልቅ ድል ተቀዳጅቷል:: "እንዴት፣ ምን አገኘ? እመለጣችሁ?"

"እንደሱ አይደለም:: ባጭሩ ነው የምነግርሽ:: የተቻላቸውን ያክል ከራሱ ጋር ተክለ ሰውነቱን ብቻ ሳይሆን መታወቂያውን ጨምሮ በሚገባ እመሳስሎ ያው እንዳልኩሽ እራሱ ሳይሆን ልዋጭ ልዋጭ በሚል ለውጬ ለውጠናል ..."

ወ/ሮ አረጋሽ ከመጠን ያለፈ ደንግጣለች:: ጥያቄዋ ግን አላቆመም:: እየተንቀጠቀጠች ቢሆንም ፣

"ይህን በማድረጉ ምን የሚያገኘው ነገር አለ?"

"ይህ በገንዘብ ከገዛው ሰውዬ እንደተረዳነው፣ የሚጠቀመው ሁለት ነገር ነው።ገንዘቡ መለቀቁን ማረጋገጥና የሚከታተለው ሰው መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ ነበር። ለማንኛውም የምንፈልገውን ወንጀለኛ ስላላገኘን ጥብቃው ለሁላችንም ያው እንዳለ ይቆያል። ስልኬ 24 ሰዓት ክፍት ነው። በይ አይዞሽ በርቺ" ብሎ ተሰነባበቱ።

ፍርዬ ትርሲትን ከሀገር ለማስወጣት ያልወጣችበት ያልወረደችበት መንገድ የለም። በስተመጨረሻ ትንሽ ተስፋ የተገኘው ግብጽ ሀገር ካይሮ ከተማ ውስጥ ለሚኖር ለአንድ ሃብታም ግሪካዊ ልጆቹን ለማሳደግ ነበር። የግሪኩ መመዘኛ ደግሞ ብዙበጣም ብዙ ነው። አብዛኛውን መመዘኛ ትርሲት የምታልፈው ቢሆንም፤ ባልየውም ሚስትየዋም ልጆቻችንን የምታሳድግልን ሠራተኛችን ሃይማኖቷ ክርስቲያን የሆነና መጽሃፍ ቅዱስ የምታውቅ መሆን አለባት" ሲሉ ሚስትዬዋ ግን "መልኳ ቀይ መሆን አለበት" ያለችው ትንሽ አስደንግጧታል።

አቶ ጊዮርጊስ ወ/ሮ ኖራን ያገቧቸው ግብፃዊ ሴት ፈልገው ሳይሆን ወ/ሮ ኖራም ሐይማኖታቸው ክርስቲያን ስለሆነ ነበር መቸስ የዚህ ዓለም ጋብቻ ሀጉና መመዘኛው ተወርቶና ተፅፎ አያልቅም እንጂው አለመነካካቱ ይሻላል። አቶ ጊዮርጊስ ከወ/ሮ ኖራ ጋር እንደተዋወቁ የወ/ሮ ኖራን ክርስቲያንነት ሲረዱ ፈፅሞ አላመኑም ነበር። ምክንያቱም ግብፅ ውስጥ የክርስቲያንነት ቁጥር እንደ ኢትዮጵያ ቀስ በቀስ ሳይሆን አየቀነሰ የመጣው በጣም በፍጥነት ነው። ከሰላሣ ዓመት በፊት 35 በመቶ የነበረው የክርስቲያን ቁጥር ዛሬ



ግብፅ ውስጥ ወደ ዘጠኝ በመቶ ወርዷል። ታዲያ አቶ ጊዮርጊስንም የገረማቸው ከዚህ አነስተኛ ቁጥር ውስጥ ወ/ሮ ኖራን ማግኘት ነበር።

ወ/ሮ ኖራ የአበዙን ፎቶ ደግመው ደጋግመው ካዩ በኋላ ያገኘውን ነገር ወደ አፉ ማለት ለሚወደው የሁለት ዓመት ልጃቸው ማይክል ነጥቆ ሳም ሲያደርገው ወዲያው ተቀበሉትና ወደ መኝታ ቤት በመሄድ ጂርጊ አረ ጂርጊ ብለው ጠሯቸውና ይህች ከኢትዮጵያ ልናመጣት ያሰብናት ልጅ መልኳ ጠይም ቢልም በጣም ቆንጆ ስለሆነች ወድጃታለሁ ቶሎ ቶሎ ብለን አናስመጣትና ተንፈስ ልበል።

አንች ከፈቀድሽ፤ አንችን ካስደሰተሽ፤ ከነገ ጀምሮ የሚያስፈልገውን አደርጋለሁ አየሽ ይህችን ልጅ ብናስመጣት ሌላው ትልቁ ጥቅማችን ኢትዮጵያዊ መሆኗ ነው፤ ኢትዮጵያዊ ሴቶች ቀጠኑም፤ ወፈሩም፤ ድኃም ሆኑ፤ ሐብታም ማንም ሊወስድባቸው የማይችለው በአመቤታችን ማሪያም አማላጅነት ከአምላካችን የተሰጣቸው ልዩ ክብር አላቸው፤ እግዚአብሔር ረድቶን ይህችን ልጅ ካመጣናት ልጆቻችን ጨዋዎች መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የአሷን ክብር እኛ ሰዎች በማናውቀውና ልንረዳው በሚከብደን መንገድ ልታስተላልፍላቸው ትችላለች፤ ብቻ በአንቺ በኩል አደራ የምለው ይህን ቆጣ ቆጣ የምትይውን ነገር ባግባቡ እንዳታደርጊው ነው። ወ/ሮ ኖራ እሽም እምቢም ሳይሉ ወደ ልጆቻቸው ክፍል ፈጠን ብለው ሄዱ።

ስሞኑን ትዝታ ለመሆኑ "ይህን ሁሉ ወሬ ከየት አመጣሽው" እባላለሁ ብላ ሳትፈራ፣ ገብረብሩክ ፖሊሶቹን የሰራቸው ሥራ በዓለም ላይ የማፈያ ሥራ የታወቁት የጣሊያኖቹ ሲሲሊዎች፣ የራሻዎቹ፣ የቡልጋሪያውያንን የሚያስንቅ ነው።

ስለ ግብረብሩክ ያለፉት ቀናት ሁኔታ የሰሙትም ያልሰሙትም ከሷ ለመስማት በመጓጓት "ምን ፈጠረ ደግሞ ልጅ" ሲሏት እስከሚያስጎነብሳት ከት ብላ እየሳቀች "መጀመሪያ እሱን መስል የሚል ጠርሙስ ለቃሚ ወይም 'ልዋጭ ልዋጭ' ከሚል ጋር ተግባባ አሉ። ከዚያ ገብረብሩክ ጠፍ በሚቆላ ምላሱ ያን ምስኪን ድሃ በአንድ ሌሊት ሃብታም እንደሚሆን አሳመነው፣ ያዘዘውን ሁሉ አሽ እንዲል አስደረገው። ከዚያም ገብረብሩክ ዘወትር የሚለብሰውን ልብስ ሳይቀይር አለበሰው። የምስኪኑ ጸጉር እንደ ገብረብሩክ ገባ አላለም ነበርና አመሳስሎ ከመሃሉ ላጨው፣ ብቻ ምን ብዬ ልንገራችሁ። እራሱን ፎቶ ኮፒ አደረገው አሉ። ከዚያ አባንክ ቤት ይህን ምስኪን ላከው። ምስኪኑ በሠላም ከወጣ ራሱ ገብቶ ብሩን ይዞ ሊወጣ፣ ምስኪኑ እዚያ ከተጨመደደችም ገብረብሩክ ከርቀት ቆሞ ሁኔታውን ያይ ነበር አሉ፣ በዚያው ጤናይስጥልኝ ደህና ሁኑ ማለት ነበር፣ እንዳሰበውም ሆነለት።"

"እኔ የምለው ትዝታዬ፣ ለውየውን ካመሳሰለ አይቀር ገንዘቡን አውጣና አምጣ ለምን አይለውም ነበር?"

"አንተ ደግሞ ገብረብሩክን የዋዛ አደረከው። ካወጣ በሁዋላ ቢቀየስበትስ፣ እንደገና ደግሞ ፊርማዬን አጥና፣ ልክ ነው አደለም ለማለት ለዚህ ሁሉ ጊዜ አጥሮት ይሆናል! አረ እኔ



ለማንኛውስ ምን አገባኝ፣ ሚስቱ ትጨነቅበት እንጅ! በሉ ልቀቁኝ የአረፍት ሰዓቴ አለቀብኝ" ብላ ወደ ቢሮዋ ገብታ ስልኳ ላይ ተጣበቀች።

አብሮ ላያቸው አናትና ልጅ አንጅ እህትማማቾች ፈጽሞ አይመሳሰሉም። አልሳቤጥ ከሥራ እንደገባች መክሰሷን ቀመስ አድርጋ አሰፋ ላይ ገደም ብላ የጀመረችውን መጽሃፍ ለማንበብ በመቻከል ገና ገለጥ ስታደርግ ከየት መጣ ከየት ሳይታወቅ የግራ ጠቋሚ ጣቱን አፉ ላይ በማድረግ በቀኝ እጁ ሽጉጡን ወደሷ በማነጣጠር "ሱሱሱ..." ሲላት "ወይ ጋሽ ገብረብሩክ እኔ ምን አደረኩ፣ እባክህን .." ብላ ስትማለደው፣ አሁንም "ሱሱሱስ.." አላትና"ነፍስሽን ከፈለግሻት፣ አድርጊ የምልሽን ብቻ አድርጊ" አሽ አለች የምትይዘው የምትጨብጠው ጠፍቷት።

ስልኳን አንስቶ ስጣትና እህትሽ ጋ ደውይና በአስቸኳይ እንድትመጣ አድርጊ። ግራ ገብቷት "ለምን እንዴት እንደዚህ ይሆናል? እዚህ ከመጣች በሁዋላ ብትጣሉስ? እህቴ አንድ ነገር ብትሆንን? እሷ ናት አስጠርታት ጉድ ያስራቻት ተብዬ ያገር መሳቂያ ልሁን እንዴ?" በጣም በመቆጣት "ሴትዮ፣ ትሰሚኛለሽ፣ ለመጥፎ ነገር አይደለም፣ ክፉ ነገር ባስብ ኖሮ እዚህ ድረስ ለምን እስመጣት ነበር። ባጭሩ እዚህ የምታስመጪት እንቺን መያዣ አድርጋ ገንዘቧን ከባንክ አውጥታእንድትሰጠኝ ነው።

"ወይ ጋሼ ገብረብሩክ፣ ገንዘብ ከሆነ፣ እኔ የፈለከውን ነገ ጥዋት አውጥቼ ልስጥህ። "በይ እባክሽ የምልሽን ፈልጊ ሴትዮ፣ ነፍስሽን ከፈለግሻት የምትይውን ብለሽ አሳምነሽ

አስመጪያት። ከዚያ እኔና አንች እቤት እንጠብቃታለን። ገንዘቤን አምጥታ ካስረከበችኝ እኔም ወደምሄድበት፣ እናንተም በሰላም ወደየቤታችሁ። ሌላ ነገር አቆሰቁሳለሁ፣ ብልጥ አሆናለሁ የሚል ካለ ቢያቅተኝ ቢያቅተኝ አንቺን ማጥፋት አያቅተኝም። ስለዚህ ያሰሽ አማራጭ የምልሽን ብቻ ማድረግ ነው።"

አንድም ቀን በሰሟ ጠርታት አታውቅም።

ሀሎ "አባዬ ኤልሳ ነኝ"

ምነው በዚህ ሰዓት ብዙ ጊዜ አትደውይም፣ ደህና ነሽ? የኔ ቆንጆ"

"አይ በጣም ደህና ነኝ። ናፍቀሽኝ ነው።"

"አረረ ..ኤልሳዬ መምህርነቱን ትተሽ ከመዲያን ልትሆኚ ነው እንዴ? "

"ምናሰበት ጥሩገንዘብ እስካገኝ ድረስ"

"ግን በደህናሽ ነው፣ አይደለም?"

"አይ ደህና እንኳን ደህና ነኝ። በጣም የማማክርሽ ጉዳይ ስላለ ብቻሽን በአስቸኳይ እንድትመጭልኝ ፈልጌ ነው።"ስልኩ ስፒከር ላይ ስለሆነ የቃል ልውውጣቸውን እንደልቡ እየሰማ ነው።

"አንቺ ልጅ ከመቸ ወዲህ ነው ነገር ማማከር የጀመርሽው? ምንድነው የሆንሽው?

"አባዬ፣ ለምን ትከራከረኛ አለሽ? ነይ ስልሽ ነይልኝ"

"እሱማ እመጣልሻለሁ፣ ነገሩን ሰማወቅ ጓጉቼ ነው እንጂ። "ግን አባዬ፣ አደራሽን ስትመጭ ማንም ሰው እንዳያውቅ ብቻሽን ነይ። "



"እሽ አልኩሽ አኮ!ግን እውነቱን ልንገርሽ ስለአስደነገጥሽኝ ደረጀ እየነዳልኝ አብረን ብንመጣስ?"

"ቆይ እንዴ ጥብቂኝ" ብላ አስልኩ ላይ ጋበ ጣለችበትና ገብረብሩክን ስታናግረው፣ "እሽ እንዲያውም ከአንድ ሁለት ነፍስ መያዣ ማግኘቱ ጥሩ ነው" አላት።

"ይቅርታ አባዬ ይሁን ያኘውና ነይ"

"በቃ ከ30 40 ደቂቃ እደርሳለሁ" ብላ ስልኩ ተዘጋ።

ያጋጣሚ ነገር ሆኖ የትዝታ የወንድሟ ሚስት ኤልሳ የምታስተምርበት የጥቁር አንበሳ ት/ቤትን ካፍቴሪያ ኮንትራት ይዛ ስለምትሠራ ከኤልሳ ጋር ጥሩ አግባብአላቸው። ገብረብሩክ በድንገት ወ/ሮ ጥሩወርቅ የምትባል ሴትዮ እናንተ ጋ የምትሠራ ታውቂያለሽ" ሲል ይጠይቃል።

"አዎ" አንጻሰችው ፡

"ቆይ ቀኗን ትጠብቅ! ብሎ ውጭ ውጪን መቃኘት ያዘ፤

እነ አረጋሽ ካሰብት ጊዜ እንዲያውም ቀደም ብለው ተከታትለው ሲገቡ ገብረብሩክ ከሁዋላቸው በመከተል "ሁለታችሁም እጃችሁን ወደላይ አድርጋችሁ ግድግዳ ተደገፉ"

"እንደተባሉት አደረጉ።ትዝታ እጆቿ ታሥረው ከሰፋው ሥር ቀጭ ብላ ሲያዩዋት ድንጋጤያቸው የባሰ ጨመረ።

"ገብረብሩክ" አለች ወ/ሮ አረጋሽ። ከት ብሎ ሳቀባት።

"ሁለት የምለምንህ ነገር፣ ብትችል አትግደለን፣ ለመግደልከወሰንክ ደግሞ እኔን እንደፈለግህ አድርገኝ፣ ይህን ምስኪን ያልፍልኛል ብሎ ጉልበቱን ሽጠ የሚያድረውንና

ኤልስዬን ምንም አታድርጋቸው። አንድ ነገር ልንገርህ ትፈቅድልኛለህ?

"ትችያለሽ፡ ፊትሽን ግን ወደኔ አታዙሪ"

"ኤልሳ፣ ምን ይበላል ምን ይጠጣል የትስ ይተኛ ይሆን፡ የት አግኝተን ገንዘብ በሰጠነው ስትልነበር።"

አሁንም ከት ብሎ ሳቀባት። ደረጀን ከእግር ጠፍሩ አስከ ራስ ጸጉሩ አተኩሮ ሲያየው የህጻን ልጅ ያክል እንኳ ጥንካሬ ይኖረዋል ብሎ ለሳልገመተ፣ አሁን ይሄን የእንግዴ ልጅ የመሰለ እንዲያገግም ብለሽ ቀጠርሽው እንጅ ይሽ ምኑም ሥራ የሚሠራ አይመስልም"

"እሽ ገብረብሩክ፣ ካልወደድከው ነገ ጥዋት አሰናብተዋለሁ።"

"እሱ የራስሽ ጉዳይ ነው። ለማንኛውም ጠባቂዎችሽ የት ደረሱ? ብለው ከተማውን ሲያምሱት እንዳያድሩ አንቺ ደውይና ሰላም እንደሆንሽና እንደምታድሪ ንገሪያቸው" ሲላት ያላትን ሁሉ አደረገች።

በጥዋት ተነስታ ባንክ ቤት ሲከፈት የባንክ ቤቱ የመጀመሪያዋ ተስተናጋጅ በመሆን ገንዘቡን አውጥታ ወለም ዘለም ሳትል ወደ ቤት ከመሄዷ በፊት እዚያው እባንክ ቤት ውስጥ እንዳለች ትብብር ጠይቃ ስልክ በመደወል

"ግሎ ገብራይ፡ ያው እንግዲህ ስውየው አፍኖ አሳድሮን አሁን ገንዘብ አምጭ ብሎኝ ገንዘብ አውጥቼ ይዤ እየሄድኩ ነው፣ ቶሎ ካልደረስኩ ኤልስዬንና ደረጀን አስይዞ ስለመጣሁ ትንሽ ኮሽታ እንኳ ከሰማ እንደሚገድላቸው ነግሮኛል።"

"ወ/ሮ አረጋሽ" አለ ገብራይ፡ እንደመቆጣትም፡ እንደመደንገጥም እያደረገው፤



ሀሉ የት ነው ያገታችሁ? ይሰማሻል?

አዎን ይሰማኛል እሁቴ ኤልሳ ቤት ውስጥ ነው፤ በል እንግዲህ መሄዴ ነው

ሀሉ ቆይ አንዴ ስሚኝ ከመሄድሽ በፊት እኛን ማግኘት አለብሽ! አላት፤...... ካገኛት በኋላ የሷን ልብስ ለብሶ እሷን ተመስሎ ገብረብሩክን ስመፋለም እያሰበ፤

ምነው ገብራይ የማይሞክረውን ልጆቹን እቤት ውስጥ ቆልፎባቸው ከርቀት እየተከታተለኝ እንደሆነስ ምኑን አውቀዋለሁ ብለህ ነው፤ ተው አባክህ ቢቀርብን ይሻለናል ብላ ሌላ ሀሳብ ጫረችበት፤

መጠርጠሩ ጥሩ ነው ግን ይህ ሰው እኮ በሽተኛ ነው፤ ገንዘቡን ከሰጠሽው በሁዋላ እንደሚለቅቻችሁ ምን ዋስትና አለ?

"በል በል ገብራይ፡ መሄድ አለብኝ፤ እግዜር ያውቃል፡ ቶሎ ልድረስላቸው" ብላ ገብራይን ከተሰናበተች በሁዋል "የእኔ እመቤት እግዚአብሄር ይስጥልኝ" ስትል አመሰገነች ለተፈቀደላት ስልክ።

ደረጀ፤.... ገብረብሩክ ወዲያ ወዲህ ሲል በዐይኑ ሲከታተለው ይቆይና ዐይን ለዐይን ግጥምጥም ሲሉ ደረጀ ከመቅጽበት ፈጽሞ የደከመ ሆኖ ጥውልግልግ ይልበታል። ቢያወጣ ቢያወርድ፡ ቢያየው ቢከታተለው አመች ሁኔታ ፈጽሞ ሊያገኝ አልቻለም። የመጀመሪያ ሙከራ ብሎ ወስነና፡ ትንሽ ራቅ ሲልለት እየተንሾካሾከ "ኤልሳ፡ ኤልሳ፡ ኸረ ይሽ ልጅ ሃይለኛ ጨንራ በሽታ አለበት ምናምን የሚበላ ልስጠው

በይው" ሲላት እንደተባለችው "ጋሼ ገብረብሩክ፣ እባክህ ፍታኝና" ብላ ጥያቄውን ስታቀርብ "ቆይ ታገሽ እህትሽ ስትመጣ አንድ ላይ ትበላላችሁ" አላት።

ወዲያውኑ "አ..አው..ው ው...ሁሁሁ" ብሎ ደረጀ ወለሉ ላይ ዝርግት ሲል ገብረብሩክ ጎትቶ ግድግዳውን አስደግፎ ሊያስቀምጠው ጎንበስ ሲል፣ "ያያጥ" አለና በቀኝ እጁ ሽጉጡን የያዘበትን ክንዱን ሲመታው ሽጉጡ ቱር ብሎ ሲወድቅ በእጁ ወዲያውኑ አገጩን ሲመታው ገብረብሩክ ጥቅልል ብሎ ዘፍ ሲል ደረጀ ሽጉጡን ለማንሳት ሲሄድ ገብረብሩክ እንደምንም ተነስቶ ከሁዋላው ባለ በሌለ ሃይሉ ሲከመርበት ደረጀ ከሥር፣ ገብረብሩክ ከላይ ሲሆኑ፣ ደረጀ የገብረብሩክ ሁለቱንም እጆቹን ከደረቱ ሥር አቅፎ ተኝቶባቸው እያፍተለተለ እያደከማቸው ነው። ገብረብሩክ እጆቹ መንቀሳቀስ ስላልቻሉ በጥርሱ የደረጀን ማጅራት ለመንከስ ይፍጨረጨራል።

አልሳ ሁለቱም እጆቿ እንደታሰሩ እንደምንም ተንጠራርታ ሽጉጡን ገብረብሩክ እንዳያገኘው በእግሯ ገፋ አደረገችና አበባ የተቀመጠበትን ሳህን እንደምንም አንስታ ከገብረብሩክ ጭንቅላት ላይ ከለከለችው። ደረጀ እንደፈለገው እንዲሆን ሆነለት አንጅ የአልሳ ዱላ ለገብረብሩክ ቅምም አላለችው። ደረጀ በመቅጽበት ዐይኑን በጣቶቹ ጓጎጠው ወዲያውኑም ሁለቱንም እጆቹን ከጥቅም ውጭ አደረጋቸው። "ኸ..ኸ..ኸ" ማለት ጀምሯል ገብረብሩክ በተራው።

ደረጀ አልሳን እንደፈታት ስልክ ወደ ፖሊስ ደውላ ቤቷ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፖሊስ በፖሊስ፣ ጋዜጠኛ በጋዜጠኛ፣ ካሜራ በካሜራ ተጥለቀለቀ።



በሀገራችን የብዙሃን የመገናኛ መስመር በሙሉየሚያወራው እየደጋገመ የገብረብሩክ በቁጥጥር ሥር መዋል ስለሆነ እነ ትርሲትም የምሥራቹን ሰምተው በጥዋት በራሪ በርረው ነው አዲስ አበባ የገቡት።

በፍርድ ቤቱ ህግናደንብ መሠረት ፖሊስ ገብረብሩክን ለፍርድ ሲያቀርብ ከሰበሰበው መረጃ ጭምር ነው። የገብረብሩክ ጉዳይ ከመጀመሪያው በቁጥጥር ሥር እስከዋለበት ጊዜ ድረስ የሚከታተለው ገብራይ ፋይሎቹን፣ የባልቻ ሆስፒታል፣ የዘውዲቱ አሟሟት፣ ሁኔታ ከወ/ት ትዝታና ከወ/ሮ ጥሩነሽ ጋር ያለው ግንኙነት፣ እንዲሁም ተበዳዮች ተማሪ ትርሲት አምባዬ፣ ተማሪ መክብብ ታምራት፣ አቶ ደረጀ ጉልላት፣ ወ/ት ኤልሳቤጥና ወ/ሮ አረጋሽ አያለ ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር ተናበበና ለቀጣዩ የፍ/ቤት ውጣ ውረድ ራሱን አዘጋጀ።

ኢትዮጵያዊ መቸስ ከአገር ውጭ ሊወጣ ሲል ከኛ የባሱ ድሃ አገሮች እንኳ በአቅማቸው የቤት ካርታና የመኪና ሊብሬ መጠየቅ ጀምረዋል። ምንያድርጉ፣ ወጥቶ የሚመለሰው በጣም ጥቂቱ ነው። አንዳንድ ሰዎች ቢቸግራቸው የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚያዘጋጀውን ሰላምታ የተባለውን መጽሄት በተለይ ወደውጭ ለሚጓዘው አትስጡ፣ ምክንያቱም ሰላምታ የሚለውን ወደሁዋላ ለታነቡት 'አትመለስ" እንደማለት ነው እያሉ ይቀልዳሉ።

እናማ ግብጾችም በእኛው ' ተደራጅተው ሲያበቁ ወደ እገራቸው ለንሄድባቸው ውጣ ውረዱ ያው ልክ አውሮፓና አሜሪካ ለንሄድ እንደምናደርገው እየሆነ ነው።

የትርሲት የግብጽ ጉዞ የተቃና እንዲሆን አቶ ጊዮርጊስ አስፈላጊውን መሰናርት አሟልተው እየተጠባበቁ ነው። በአገር ውስጥ ስላለው ውጣ ውረድ ደግሞ የፍርድ ቤቱን ጣጣ ከጨረሰች ጀምሮ በነቢዩ እርዳታ ወደመጠናቀቁ ደርሷል።

እንባ ሳይሆን የደም እንባ በትርሲትና በመክብብ ህይን ላይ መፍሰስ ከጀመረ ከረምረም ብሏል። ሞት ካለያቸው በስተቀር ምንም ሃይል እንደማይለያቸው፣ ሃይለኛ ቃልኪዳን እንዳላቸው ሁኔታው ሁሉ ይመሰክራል። ግን አንዳንዴም፣ በተለይ ከአቅም በላይ በሆነ ነገር ቃል ሲታጠፍ ይታያል። የዚህ ዓለም ሕዝብ ሲምል ሲገዘት፣ ካላንተ ካላንቺ ሲባባሉ ይኖሩና የተፋቀረው ሲጣላ፣ የተጣላው ሲዋደድ ማየት ደግሞ እንዲሁ ይስተዋላል። ፖለቲከኞችም ከዚህ በመነሳት ይመስላል 'በፖለቲክ የረጅምጊዜ ጠላት ወይም ወዳጅ የለም' የሚሉት። የእነ ትርሲት ሁኔታ ግን ከተዋወቁበት እስካሁን የተጓዙበትን ጠመዝማዛ የህይወት ጎዳ ሮልብ ብሎ ለተከታተለው፣ የልዩ ኢዮቤልዮ ሽልማት ቢኖረው ኖሮ አለምንም ተቀናቃኝ ይወስዱት ነበር፡ እወጡ አወረዱ፤ በሁሉም አቅጣጫ ሞከሩ፤ የትርሲትን የግብጽ ጉዞ የሚያስቀር ግን ከቶ ሊያገኙ አልቻሉም።

'እግዜር ሳይደግስ ..' እንደሚባለው በተለይ መክብብ ትንሽ ተንፈስ የሚለው በቴዲ አፍሮ ተገጥሞ በማዲንጎ አፈወርቅ የተዜመውን "ከተለያየንም ምን አደርጋለሁ"ን ሲሰማ ነው።

ማዲንጎ የንብ አውራ የዋጠ በሚመስለው ድምፁ



ከተለያየን ምን አደርጋለሁ እችለዋለሁ፤
አብረን ባለን ግዜ ብዙ አሳልፈናል፤
የመለየት እንባ ፊቴን እያራሰው ፤
ልሸኝሽ ጨክኜ የምወድሽን ሰው ፤
ሰው ወዶ ሰው እንደመለየት ከፉ ነገር የለም፤
ልሸኝሽ የመጨረሽያየን በይ ይሁን ግድ የለም፤
ጨክኜ ስሸኝሽ በይ ጨክነሽ ሂጂ፤
ሰው ባሰው አይሆንም በሱ ፈቃድ እንጂ፤
ቅር ይላል ከሚወዱት ጋራ ጨክነው ሲለዩ፤
ያቅታል ወደፊት ለመሄድ ወደሁዋላ እያዩ፤

የሚለውን ከለማ በሁዋላ "እንዲያው ቴዲና ማዲንጎን የት ባገኘሁዋቸው፣ የሚገርም ነው፣ ለእኔ እኮ ነው የዘፈኑት፣ እፍፍፍፍ ..እነዚህስ የሕዝብ ሃብት ናቸው"ይላቸዋል።

አቶ ገብሩን ለመለናበት እና ምርቃታቸውን ለማግኘት ከሂዱ ጀምሮ እንደባለፈው ብዙ ቀናቶች መቆየት ባይችሉም ያላቸውን ጊዜ ለማበቃቃት ተፍ ተፍ እያሉ ሲሆን፣ አቶ ገብሩ እንዲ ጨዋታ ከጀመሩ ባጭር ጊዜ ውስጥ ስለማይለቁ የተቻላቸውን ያህል በትእግስት ለማዳመጥ ቀደም ብለው ተዘጋጅተዋል።

"እሽ የኔ ልጅ፣ ግብጽ ልሄድ ነው እልሽኝ? ግን በተገቢው መንገድ እስበሸበታል? ከዘመድ አዝማዱ ጋርስ በደንብ መክረሽበርታል? 'ተመካክረው ያደረጉት ነገር' እንደሚባለው ማለቴ ነው።"

"ልክ ነዎት አባባ ያሉትን ነገር ሁሉ እድርጌያለሁ።"

"ይሁን እንግዲህ፣ ግብጾች ብቻ ሳይሆኑ የእኛን ታሪክ እያንኳሰሱ የእነሱን ብቻ ከፍ ከፍ የሚያደርጉት፣ ሀገሮች ሁሉ ወደ እኛዋ ኢትዮጵያ አንድ ቀን ይሰደዱ ይሆናል:: ምን ይደረግ እንግዲህ፣ አቡን ገብረ መንፈስ ቅዱስ ይከተሉሽ:: ሺ በአክናፉ ቅዱስ ሚካኤል የቀልቢው ገብረኤል ሌት ተቀን ይጠብቁሽ፡ አንድ ሳልረሳው የምነግርሽ ነገር ቢኖር በምንም ሀይነት መንገድ የአባይን ወንዝ በተመለከተ ውይይት(ክርክር) ቢያነሱብሽ ምንም የምታውቂው ነገር እንደሌለ ከማስረዳት በስተቀር ትንፍሽ እንዳትይ:: "በእናንተ ተንኮል የደከመችው ኢትዮጵያ ከጠነከረች ነገ የሀባይን ጥያቄ እንስተን ያኔ ማን እንደሆነ ባስታሪኩ እንተያያለን፣..." የመሳሰሉትን የምትይ ከሆነ 'ይህች ጥሬ ካደረች..' ብለው ይተርቱብሻል:: ወይም ዓለም እያወቀው በመጣው "ጠላትህን ለማጥፋት ከፈለግህ ጓደኛህ አድርገው" የሚለውን የተንኮል ትረታቸውን በእንቺ ላይ ተፈጻሚ ሊያደርጉት ይችላሉ::"

"ይገርማችሁዋል ከዚህ በፊት ደጋግማችሁ ሰምታችሁት ሊሆን ይችላል:: ጳጳስ እንኳን ከራሳችን ዜጋ እንዲኖረን ስለማይፈልጉ፣ በሃይማኖት ስበብ ሲያሞኙን ጳጳስም እነሱ ነበሩ የሚልኩልን:: እቤት! ቀደም ብላችሁ ተፈጥራችሁ ቢሆን ኖሮ ስንት ቀልማዳ ነገር ከግብጽ የሃይማኖት ትምህርት የተማሩት አስተማሪዎች የሚያስትምሩትን ትሰሙ ነበር:: ምንም ሳያፍሩ ሀባይን እምላካችን በኪን ጥበቡ ለግብጽ እንደፈጠረላቸውም ይናገሩ ነበር:: ነገር አበዛሁባችሁ እንጅ፣ ጥንት ግብጾችን ብቻ ሳይሆን እዚያ አካባ ያሉ እገሮችን



ጨምራ ኢትዮጵያ ታስተዳድር እንደነበረ ብዙ መረጃዎች አሉ::

ይሁን መቾም፣ 'ታሪክ ራሱን በራሱ ይደግማል' ይባል የለ፣ ቅድም እንዳልኳችሁ ይሆን ይሆናል::

እኔ የምልህ የእኔ ልጅ፣ ነቢዩ ያልከው ሰው እንዲያው ምን ቢያሳስበው ነው ይህን ያህል ውለታ የጣለብኝ? እራሴን እስከሚያመኝ ባስበው ባስላስለው መልኩን ሳስታውሰው አልቻልኩም:: ስለኔ ያጫወተህ ታሪክ ግን በሙሉ እውነት ነው:: ያው ከዚህ አካባቢ ብዙ ተማሪዎችን አውቅ ስለነበረ የትኛው እንደሆነ ግን አላወቅሁትም:: ለማንኛውም እኔን እንዳስታወሰከኝ ሳንተም አስታዋሽ ይዘዝልህ፣ የሰው ትልቅነቱ ወደ ሁዋላ መለስ ብሎ ያለውፈው ህይወቱን ለማስታወስና የላላውን ማጥበቁ፣ የጠበቀውም እንዳይላላ ማድረጉ ነው:: እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ከሥራ ሥሮቼ መድከም በስተቀር ጤናዬ በጣም ደህና ነው::አይዞህ የኔ ልጅ ስለኔ ብዙም አታስብ:: ኑሮዬም ደህና ነው:: አንድ ነገር በአባትነቴ ኮርቼ የማስቸግርህ ነገር ቢኖር እዚህ ሽንኩራ ውስጥ አንድ እንኳን ከፍ ያለ ት/ቤት ስለሌለ ጓደኞችህንም ሆነ መንግሥትን ትብብር ጠይቀህ ልጆቻችን ትምህርት ፍለጋ ከሚንከራተቱ አንድ ቁም ነገር አድርግ በልና ንገረው:: መልእክቱን አበዛሁብህ ልበል? አደራ እንዳትረሳው፣ ከተቀመጥክበት ብድግ ብለህ መልእክቴን እድርስልኝ::"

"ኧረ ግድ የለም አባባ፤ የት/ቤቱን ነገርማ እኔም እእምሮ ውስጥ ሁሌም የሚጉላላ ስለሆነ በደንብ አድርጌ ነው የምነግረው::"

"ጎሽ! ተባረክ፣ አንቺም ተባረኪ! እንትፍ እንትፍትፍትፍ ..." አሉባቸው። "እንድምንም ብለህም ሳልሞት ብንተያይና ብመርቅህ ደስ ይለኛል" በልልኝ

# ምዕራፍ ስምንት

"የተከበራችሁ መንገደኞቻችን በካፒቴን በርይሁን እና በሥራ ባልደረቦቹ ስም ሆኜ እንኳን ደህና መጣችሁ እላለሁ። ይህ የበረራ ቁጥር 677 ነው። የምንበርበትም ከፍታ 35 ሺህ ጫማ ሲሆን በቀጥታ ወደ ካይሮ እናመራለን። የምንደርስበት ጊዜ በካይሮ ሰዓት አቆጣጠር ከስዓት በሁዋላ 8 ሰዓት ይሆናል። መልካም በረራ።"

ከሽንኮራ እንደመጣች ብዙም ሳትቆይ፣ ወዳጆቿን መሰነባብቱ፣ እንዱን ስትይዝ እንዱን ስትለቅ በቂ እንቅልፍ ማጣት ከጀመረች ከረምረም ስላለች አውሮፕላኑ ወደ ሚፈለግበት ከፍታ ደርሶ መምዘግዘግ ሲጀምር፣ ትርሲት ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወሰዳት። ወደ ካይሮ ስትቃረብ ቀበቶዋን እንድትጣጠቅ እና ወደላይ የለጠጠችውን ወንበር እንድታቀና የበረራ እስተናጋጇ ስትቀሰቅሳት፣ አጠገቧ የተቀመጡት ሴት ወይዘሮ ውይ "ታድለሽ እኔ ምን ቢደክመኝ፣ ምን ረዥም በረራ ብበር እንቅልፍ ዝር አይልብኝም። የሚገርም ነው፣ ጭራሽ ከጀል አያደርገኝምኮ።"

"አይ፣ እኔ የመጀመሪያዬ ስለሆነ ይሆናል።"



"ኧረ! ልክ ነሽ! ሊሆን ይችላል፣ ውይ፣ የኛስ አውሮፕላን ላይ መንጠልጠል በዛ። እንንዴማ በሳምንት 2 እና 3 እገር የምሄድበትም ጊዜ አለ።"

"ዋው! ትኬቱ አይወደድብዎትም?"

"ከመግዛትስ ገላግሎኛል፣ ባለቤቴ ኢትዮጵያ አየር ላይንስ ስለሚሠራ በሱ ነጻ ቲኬት ነው ዓለምን የምዞረው።"

"በየሄዱበት አገርስ ዘመድ አለዎት?"

"አንዳንድ አገር ዘመድም ጓደኛም ይኖራል። ግን ለአልቤርጎ የምናወጣውን ወጭ ይቀንስልናል ብለን እስው ጋ መቆየት ጉዳት አለው።"

ትርሲት ሳቅ ብላ "በነጻ መቆየት ጉዳት አለው ማለት ነው?"

"እንዴት መሰለሽ፣ እዘመድ ወይም ጓደኛ ጋ ከቆየሽ፣ ያቺንአንድ ቀን ወይም ሁለት ቀን የቆየሽባትን እንደ ትልቅ ነገር ቆጥረው ለዘመዶቻቸው እቃ ያሸክሙናል። የነሱን እቃ ከተሸከምን ደግሞ ምኑን እተረፍነው?"

"የት ሰፈር ነው ንግድዎት?"

"ንግድ ስልሽ እኮ አየር ባየር ከጉምሩክ ሠራተኞች፣ ከትኬት ኤጀንቶች ከሆስተሶች ጋር እየተዛመድን፣ መንግሥትም ቀረጥ ክፈሉ እያለ እንዳያስቃየን የተለያዩ ዘዴ እየተጠቀምን የሩጫ የድብብቆሽ ንግድ ነው። ብታይው እየር ባየር ንግድ እንዴት በጣም ከባድ መስላሽ፤ እግዚአብሄር የረገመው ተረኛ የጉምሩክ ፊታሽ ካጋጠመን ደግሞ ድካማችን ሁሉ መና መቅረቱ ነው።"